# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የአካባቢ ፓሊሲ

በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን
ከኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚ/ር ጋር በመተባበር የተዘጋጀ

አዲስ አበባ

መጋቢት 24 ቀን 1989

መግቢያ

የኢትዮጵያ የእንክብካቤ ስልት ተፈጥሮአዊ፣ ሰው ሰራሽ እና ባሕላዊ ስለሆኑ ሀብቶችና በነሱ ስላለን የአጠቃቀም ብቃትና ጉድለት የተዋሀደ አንድ ወጥ አመለካከት ያለው ሲሆን ከአካባቢ ዘላቂነት ጋር የተዛመዱ በሥራ ላይ ያሉና ለወደፊት የታለሙ ዕቅዶችን፣ ፓሊሲዎችንና ኢንቨስትመንቶችን አንድ ወጥ በሆነ ማዕቀፍ ለማቀናጀት ጥረት ያደርጋል።

የኢትዮጵያ የእንክብካቤ ስልት አቀራረጽ በሶስት ወቅቶች የተካሄደ ሲሆን ሥራው የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1989 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማህበር (IUCN) መካከል የመጀመሪያው የኘሮጀክት ስምምነት ከተፈረመ በኃላ ነበር።

አንደኛ ወቅት (እ.ኤ.አ ከ1989-1990)- ይህ የመጀመሪያ ወቅት ለኢትዮጵያ የእንክብካቤ ስልት የጽንሰ ሀሳብ መሰረት የሚሆን ረቂቅ የተዘጋጀበት ሲሆን ረቂቁ ያተኮረው ቁልፍ የሆኑ የአካባቢና የልማት ጉዳዮችን በመለየት ላይ ነበር።

ሁለተኛ ወቅት (እ.ኤ.አ ከ1990-1998)- ይህ ሁለተኛው የስልቱ ዝግጅት ወቅት የኢትዮጵያ የእንክብካቤ ስልትን ፓሊሲ፣ ተቋማዊ መዋቅርና እና የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት ላይ ያተኮረ ነበር።

ሶስተኛ ወቅት (እ.ኤ.አ ከ1995-1998)- ይህ በመካሄድ ላይ የለና ዐቢያ ትኩረቱም የክልሎችን አቅም መገንባት ሲሆን፣ የክልል መስተዳድሮች የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ የድርጊት መርሃ ግብሮችና የልማት ኘሮግራሞች የሚጠናቀቁበትና ሥራ ላይ መዋል የሚጀምሩበት ክፍል ነው።

የኢትዮጵያ እንክብካቤና ስልት ሠነድ /ዶኩመንት/ በአምስት ጥራዞች ተዘጋጅቷል። ጥራዝ አንድ፣ የተፈጥሮ ሀብት መሠረት፣ ጥራዝ ሁለት፣ ፓሊሲና ስልት፣ ጥራዝ

ሶስት፣ ተቋማዊ መዋቅር፣ ጥራዝ አራት፣ የድርጊት መርሃ ግብር እና ጥራዝ አምስት የኢንቨስትመንት መርሃ ግብር ጥንቅር ናቸው፡፡

ይህ የኢትዮጵያ የአካባቢ ፓሊሲ ከኢትዮጵያ እንክብካቤ ስልት ሠነድ ጥራዝ 2 የተወሰደ ሲሆን በአካባቢ ጥበቃ ባልሥልጣንና በተለያዩ ዘርፎች የሚካሄዱትንና መካሄድ ያለባቸውን አካባቢ ነክ ተግባራት ለመምራት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ ፓሊሲ በኢትዮጵያ እንክብካቤ ስልት የፓሊሲ ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡

ዝርዝር ስልቶችና ስልቶቹ የተመሰረቱባቸው አጫጭር የሁኔታ መግለጫዎችና ዓላማዎች በኢትዮጵያ እንክብካቤ ስልት የተለያዩ ጥራዞች ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ይህ የኢትዮጵያ የአካባቢ ፓሊሲ መጋቢት 24 ቀን 1989 በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀደቀ፡፡

# የኢትዮጵያ የአካባቢ ፓሊሲ

## 1. የተፈጥሮ ሀብት መሠረትና የፖሊሲው አስፈላጊነት

### 1.1 የተፈጥሮ ሀብት መሠረትና የገጠሩ አካባቢ

የተፈጥሮ ሀብቶች የኢኮኖሚ መሠረት ናቸው። የአነስተኛ አርሶ አደሮች ግብርና፣ በአንዳንድ ቦታዎች ውስጥ የደን ሥራን ጨምሮ፣ ከጠቅላላው የአገር ውስጥ ምርት ወደ 45 በመቶ፣ ከውጭ ንግድ 85 በመቶ፣ እና ከሥራ ቅጥር 80 በመቶውን የያዘ ዋነኛ ዘርፍ ነው። በፓሊሲ ድክመት፣ በተደጋጋሚ ድርቅ፣ በእርስ በርስ ጦርነት፣ በተፈጥሮ ሀብት መመናመንና በመሠረተ ልማት ብቃት ዝቅተኝነት ምክንያት የግብርና ምርት አለመጨመር የኢኮኖሚው የጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት ላለመጨመርና መዋዠቅ ዋና መንስኤ ሆኖ ቆይቶአል።

መሠረታዊ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የልብስና የመጠለያ ፍላጎቶችን የሚያሟሉት ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች (Renewable Natural Resource) እንደመሬት፣ ውሃ፣ ደኖችን ዛፎች እንዲሁም ሌሎች የብዝሀ ሕይወት (Bio-diversity) ዓይነቶች፣ ጥራታቸው አሽቆልቁሎ ዝቅተኛ የምርታማነት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። በብዙዎቹ የኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች በአሁኑ ወቅት ያለው የእንጨት ፍጆታ የተፈጥሮ ደኖች ራሳቸውን ከሚተኩበት የምርት መጠን ይበልጣል። በአብዛኛው በዝናብ የሚጠቀም ግብርናን ለማስፋፋት የሚጨፈጨፈው የደን መሬት መጠን ከ80,000 ሄክታር እስከ 200,000 ሄክታር በዓመት እንደሚሆን ይገመታል።

ፍግ አፈርን እንዲያዳብር በማድረግ ፈንታ በከብትነት መቃጠሉ፣ በዓመት ለ550,000 ቶን የእህል ምርት ቅነሳ ምክንያት እንደሆነ ይገመታል። እ.ኤ.አ. በ1990 ሰው ሰራሽ የአፈር መከላት በዓመት ወደ 40,000 ቶን የሚገመት የእህል ምርት እንዳይገኝ አድርል፣ ቁጥጥር ካልተደረገበት ይህ መጠን እ.ኤ.አ በ2010 ወደ 170,000 ቶን ይደርሳል። የቤት እንስሳት በገጠርና በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ሚና

ይጫወታሉ፣ ይሁንና ከዚህ በፊት በተሰጠው ግምት መሠረት እ.ኤ.አ በ1985 እና በ1995 መካከል 2 ሚሊዮን ሄክታር የሚሆን የግጦሽ መሬት በአፈር መከላት ጠፍቷል። የመሬት ሀብት መመናመን እ.ኤ.አ በ1990 መጠኑ 1.1 ሚሊዮን ትሮፒካል ላይቭስቶክ ዩኒትስ (TLUs) የሚሆን ዓመታዊ የቤት እንስሳት ምርት ቅነሳ እንደሚያስከትል ሲገመት፣ ሁኔታው ቁጥጥር ካልተደረገበት የምርት ማሽቆልቆሉ እ.ኤ.አ በ2010 ወደ 2.0 ሚሊዮን (TLUs) ወይም አሁን ካለው የአገሪቷ የከብት ብዛት ወደ 10 በመቶ ያህል ይሆናል።

ከኢኮኖሚ አንፃር ሲታይ፣ እ.ኤ.አ በ1990 በአፈር መከላት ምክንያት ሳይገኝ የቀረው የግብርና ምርት (ማለትም አዝመራና የቤት እንስሳት) በዋጋ ሲተመን (እ.ኤ.አ በ1985 ዋጋ) ወደ ብር 40 ሚሊዮን እንደሚሆን ሲገመት፣ ከብትንና አገዳን በማገዶነት የማቃጠል ዋጋ ደግሞ ወደ ብር 650 ሚሊዮን ይደርሳል። ስለሆነም በግዑዛዊና (በፊዚካላዊ) ስነ ሕይወታዊ (Biological) ምክንያቶች አፈር መመናመኑ እ.ኤ.አ በ1990 ሊገኝ ይችል ከነበረው ጠቅላለ የአገር ውስጥ ምርት ወደ 17 በመቶ የሚሆነው ሳይገኝ ቀርቷል።

እ.ኤ.አ. በ1990 በአፈር መከላት ሳቢያ ለዘለቄታው የጠፋው የአገሪቷ የአፈር ንብረት በዋጋ ሲተመን ብር 59 ሚሊዮን እንደሚሆን ተገምቷል። በዚህ መጠን ነው የአገሪቱ የአፈር ንብረት (Soil Capital) በብሔራዊ የኢኮኖሚ ስሌት (National Accounts) ውስጥ ገብቶ የአፈር መባከን ከአገሪቷ የተጣራ ብሔራዊ ገቢ (Net National Income ላይ መቀነስ ያለበት።

የኢትዮጵያ የደን ልማት የድርጊት መርሐ ግብር(EFAP) እ.ኤ.አ በ1990 የነበረው የደን መመናመን ሙሉ የዋጋ ስሌት ወደ ብር 138 ሚሊዮን፣ ወይም ሊገኝ ከነበረው ብር 544 ሚሊዮን ጠቅላላ የአገር ውስጥ የደን ውጤት ምርት ውስጥ ( Forestry GDP) ወደ 25 በመቶ እንደሚሆን ገምቷል።

ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የማዕድን ሀብቶች በመጠንና በጥራት ቢኖሩም፣ በአሁኑ ወቅት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ከጠቅላላው የአገር ውስጥ ወደ 2 በመቶ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ለመስኖ፣ ለግብርናና ለውሃ ኃይል ማመንጫ ካላት ከፍተኛ የውሃ ሀብት 1 በመቶው ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል። የኃይሉ ዘርፍ ከዓለም በአነስተኛ ደረጃ ካለሙት አንዱ ሲሆን፣ የሀገሪቱ የኃይል ፍላጎት 90 በመቶው የሚሟላው ከዕፅዋት ክምችት ከሚገኝ ማገዶ (Biomass fuel) ፣ በተለይም ከእንጨት፣ ከከሰልና ከእንስሳት ኩበት ነው። የኢትዮጵያ የአዝርእትና የብርቅ ዕፀዋትና እንስሳት ዝርያዎች ብዛት ረጅም ታሪክ ባለው የመንግስት ጣልቃ ገብነትና የህዝብ ተሳትፎ መዳከም እንዲሁም በህዝብ ብዛትና በግብርና ማስፋፋት ምክንያት እየቀነስ ነው።

### 1.2 የከተሞች አካባቢ

የወቅቱ የከተሞች ሕዝብ መጠን ከአጠቃላዩ የህዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር 15 በመቶ ብቻ ነው። ዓመታዊ ዕድገቱ ግን 5.4 በመቶ ነው። ይህ ዓመታዊ ዕድገት እ.ኤ.አ. በ2020 ወደ 30 በመቶ ሊደርስ ይችላል።

በአሁኑ ወቅት የከተሞች መኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ብቃት የሌለው በጣም ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ያለው ነው። በአዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙት መኖሪያ ቤቶች ወደ 31 በመቶ የሚሆኑት የንፅህና መገልግያዎች የሌሏቸው ሲሆኑ፣ በሌሎች ከተሞች አካባቢዎች ይህ መጠን ወደ 48 በመቶ ይደርሳል። የንፅህና አገልግሎቶች ያለመሟላት፣ ተገቢ የፍሳሽ አገልግሎት መሠረተ ልማቶች አለመኖርና በከተሞች ውስጥ እንደፈለጉ መፀዳዳት አደገኛ የጤናና የአካባቢ ችግሮችን ፈጥረዋል። በአዲስ አበባና በሌሎች ትላልቅ የከተማ ማዕከሎች አቅራቢያ የሚገኙት ወንዞችና ትናንሽ ዥረቶች እንደ ክፍት የፍሳሽ ቦዮች በማገልገላቸው የተቅማጥና የሌሎች በሽታዎች ዋነኛ ምንጮች ሆነዋል። በርካታ መፀዳጃ ቤቶች የብዙ ሰዎች የጋራ መጠቀሚያ በመሆናቸውና ብዙውን ጊዜ መዝጊያ እንኳን ስለማይኖራቸው ለመፀዳዳት አመቺ አይደሉም።

### 1.3 ተፈጥሮአዊና ባህላዊ ቅርሶች

የኢትዮጵያ ከፍተኛ ተፈጥሮአዊና ባህላዊ ቅርሶች በእያንዳንዱ ሰው የዕለት ተዕለት ኑሮ ሁኔታ ውስጥ ዘልቀው ይታያሉ። በመሆኑም ለብሔራዊ ስሜት ጥንካሬና ለማህበራዊ ውህደት ኃይል ይሰጣሉ። ለአገር ጎብኝዎችም ዋና መስህብ መሆን ስለሚችሉ የቱሪስት

ኢንዱስትሪን ከማልማት አኳያ እጅግ ጠቃሚ ናቸው። ሆኖም አብዛኛው ቅርስና ባህል በእንክብካቤ ጉድለት፣ በመሰረቅ ወይም በመጐዳት እንዲሁም በግልጽ በማይታዩና በማይዳሰሱ ተለዋዋጭ ማህበራዊና ባህላዊ ዕሴቶች፣ በባዕድ አመለካከቶችና አገር ውስጥ በገቡ ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት በመጐሳቆል ላይ ይገኛሉ።

### 1.4 የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ፖሊሲ አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ /ኢፌዴሪ/ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲና (Macro-Economic policy) ሥልት ማዕቀፍ አዘጋጅቷል። የዘርፍ ልማት ፖሊሲዎችና ሥልቶች ተቀርፀዋል ወይም በመቀረፅ ላይ ናቸው። በሕገ መንግሥቱና በብሔራዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲው ውስጥ የአካባቢ ዘላቂነት ኢትዮጵያ ለምታካሂደው የልማት እንቅስቃሴ ስኬት እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ዕውቅና አግኝቷል። ሆኖም እነዚህን አጠቃላይ አቅጣጫዎች በዝርዝር የሚያሳይና የተፈጥሮ ሀብትንና የአካባቢን አጠቃቀምና አያያዝ በማቀናጀት ወደ ዘላቂ ልማት የሚመራ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ አጠቃላይ የፖሊሲ ማዕቀፍ እስከ አሁን አልነበረም። ስለዚህ አገሪቷ አሁን ከምትገኝበት የፖለቲካና የፖሊሲ ደረጃ አኳያ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ አጠቃላይ ፖሊስ መቅረጽ ወቅታዊ ነው።

## 2. የፖሊሲ ግብ፣ አላማዎችና መርሆዎች

### 2.1 አጠቃላይ የፖሊሲ ግብ

አጠቃላይ የፖሊሲው ግብ የኢትዮጵያውያንን ጤንነትና የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል፣ ለማሳደግና የወደፊት ትውልዶች ፍላጎቶቻቸውን መሟላት የሚኖራቸውን አቅም ከአሁኑ ትውልድ ፍላጎቶች መሟላት ጋር ለማቻቻል፣ በአጠቃላይ አስተማማኝ በሆነ የተፈጥሮአዊ፣ የሰው ሠራሽ፣ የባህላዊ ሀብትና የአካባቢ አያያዝና አጠቃቀም አማካኝነት ዘላቂ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማትን ማራመድ ነው።

## 2.2 የፓሊሰው ዝርዝር ዓላማዎች

የፓሊሲው ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. መሠረታዊ የሆኑ ሥርዓተ መሕድራዊ (Ecological) ሂደቶችንና የሕይወት ምሰሶ የሆኑ ደጋፊ ሥርዓቶችን ቀጣይነት ማረጋጥ፣ ብዝሃ ሕይወት (Biological Diversity) እንዲጠበቅና ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች (Renewable Natural Resources) እንደገና የማቆጥቆጥና የመበራከት ችሎታቸው በሚጠበቅበትና ቢቻልም በሚጐለበትበት ሁኔታ እንዲሁም የመጭው ትውልድ ፍላጎት እርካታ አጠያያቂ በማይሆንበት መንገድ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋጥ፣ እንደገና የማቆጥቆጥና የመበራከት ችሎታቸው በተዳከመበት ቦታ አግባብ ባላቸው የዕርምት እርምጃዎች አማካኝነት መልሰው የሚያንሰራሩበት ሁኔታ መሻት፣

ለ. ከማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብቶች (Non-Renewable Natural Resources) የሚገኘው ጥቅም እስከተቻለ ድረስ ለረዥም ጊዜ እንዲቀጥል መደረጉን ማረጋገጥና በጥቅም ሲውሉ በሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች እንዲሁም በአካባቢ አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ መቀነስ፣

ሐ. በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በመገለገል እና/ ወይም እስከ አሁን በሚገባ ያልተስፋፉ ወይም ጭራሹኑ ያልታወቁ አጠቃቀሞችን በመሻት፣ በአሁኑ ወቅት በዝቅተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ የዋሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች ለይቶ ማወቅና ማልማት፣

መ. የአካባቢንና ከአካባቢ የሚገኙ አገልግሎቶችን እሴት አጠቃላይ የዋጋ ተመን በማውጣትና፣ በአሁኑ ወቅት በገንዘብ ሊተመኑ የማይቻሉ ማኀበራዊና አካባቢያዊ ወጪዎችንና ጠቃሜታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማትን ሙሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ወጪዎችንና ጠቀሜታዎችን በዕቅድ፣ በአፈጻጸምና በሂሳብ ስሌት ሂደቶች ውስጥ ማካተት፣

ሠ. የነዋሪዎችን አካላዊ፣ ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ሌሎች ፍላጐቶችን ዘላቂነት ባለው መንገድ ለማርካት የሕዝብ ሠፈራ ቦታዎችን አካባቢ ማሻሻል፣

ረ. ውጤታማ ለሆኑ የመከላከያ ዕርምጃዎች የሚደረገው ወጪ ከሚገኘው ጠቀሜታ ሳይበልጥ፣ የመሬት፣ የአየርና የውሃ ብክለትን በተገቢ ወጪ (Cost-effective way) መከላከል፣

ሰ. የኢትዮጵያ የበለፀጉና የተለያዩ የወግና የባህል ቅርሶች መንከባከብ፣ ማልማት፣ ዘላቂነት ባለው መንገድ መምራትና ድጋፍ መስጠት፣

ሸ. በአካባቢ አያያዝ የሕዝብን ሥልጣን እውን ማድረግና የሕዝብንና የሕዝብ ድርጅቶችን ተሳትፎና የአመራር ክህሎት በሁሉም ደረጃ ማሳደግ፣

ቀ. በአካባቢና በልማት መካከል ያሉትን ወሳኝ ግንኙነቶች በሚመለከት የሕዝብ ግንዛቤ እንዲጐለብት ማድረግና ንቃትን ማዳበር።

### 2.3 ቁልፍ መርሆዎች

ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሰው አጠቃላይ የፓሊሲ ዓላማዎች በስተጀርባ በርከት ያሉ ቁልፍ መርሆዎች ይገኛሉ። እነዚህን አጠቃላይ የሆኑ መርሆዎች መንደፍና በግልጽ ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በተከታታይ የሚነደፈውን ፓሊሲ፣ ሥልትና የመርሐ ግብር ዝግጅትንና አፈጻጸምን ቅርጽ ያስይዛሉ። በመሆኑም የዘርፎችና የሌሎች በርካታ መድበለ ዘርፍ (Cross-Sectoral) ፓሊሲዎች እንዲሁም አካባቢን የሚመለከቱ ሌሎች ፓሊሲዎች ከእነዚህ መርሆች አንፃር ይገመገማሉ።

**ቁልፍ የሆኑት መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው።**

ሀ. እያንዳንዱ ሰው በጤናማ አካባቢ የመኖር መብት አለው፣

ለ. ሰላምና የግል ደህንነት በሌሉበት ዘላቂ የአካባቢ ሁኔታና የኢኮኖሚ ምርት ሥርዓቶች ሊኖሩ አይችሉም። እነዚህ ሁኔታዎች እንዲኖሩ ማኅበረሰቦች ሕይወታቸውንና አካባቢያቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችላቸውን ሥልጣን መጨበጣቸው ይረጋገጣል፣

ሐ. የታዳሽ ሀብቶች (Renewable Resources) ልማት፣ አጠቃቀምና አያያዝ ዘላቂ እንዲሆን ይደረጋል፣

መ. የማይታደሱ ሀብቶች አጠቃቀም እስከተቻለ ድረስ ባነሰ መጠን እንዲሆን በማድረግ ጥቅም የሚሰጡበት ጊዜ ይራዘማል፣ (ለምሳሌ፣ ጥቅም ላይ የዋሉ ሀብቶችን መልሶ እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ) (Recycling)፣

ሠ. ታዳሽና የማይታደሱ ሀብቶች በቅልጥፍናና በተገቢው መንገድ በአገልግሎት ላይ በሚያውሉ አግባብ ባላቸውና ዋጋቸው ከመግዛት አቅም ጋር በሚመጣጠን

ቴክኖሎጂዎች መጠቀም፣ ከለውጦች ጋር ማጣጣም፣ ማሳደግና ማሰራጨት ያስፈልጋል፣

ረ. በአጭር ጊዜ የኢኮኖሚ ዕድገትና በረዥም ጊዜ የአካባቢ ጥበቃ ተፃራሪ ፍላጎቶች መካከል መቻቻል እንዲኖር በሚያስፈልግበት ጊዜ የልማት እንቅስቃሴዎች ሥነ መሕድራዊና ሕይወት ደጋፊ በሆኑ ሥርዓቶች ላይ የሚደርሷቸው የማመናመንና የመበከል ተፅዕኖ እስከተቻለ ድረስ ማነስ አለበት። ምክንያቱም የተመናመነ አካባቢን እንደገና ማቋቋም በጣም ከባድ ወጪን የሚያስከትል ሲሆን የጠፉ ዝርያን እንደገና መልሶ ማምጣት ደግሞ ጭራሹን የማይቻል በመሆኑ ነው። ስለሆነም ልማትንና አካባቢን ለማቻቻል በተቻለ መጠን ወደ ጥንቃቄው ማዘንበሉ የሚመረጥ ይሆናል፣

ሰ. በመመናመን ወይም በብክለት ምክንያት በሀብት ወይም በአካባቢ ላይ በሚደርሱ ጉዳቶች ምክንያት የሚፈጠሩ የአካባቢና የማኀበራዊ ወጪዎች በሙሉ (ወይም የታለፉ ወይም የቀሩ ጥቅሞች) በመንግሥትና በግል ዘርፍ ዕቅድና ስሌት (Accounting) ውስጥ መካተት ይኖርባቸዋል፣ ውሳኔዎችም እነዚህን ወጪዎች በማሳነስ ላይ ይመሠረታሉ፣

ሸ. የተፈጥሮአዊ፣ የሰው ሠራሽና የባህላዊ ሀብቶችን ዋጋ ተመን የሚያዛቡ የገበያ ስርዓት ድክመቶችንና የቁጥጥር እርምጃዎችን ለማረም የተጠቃሚ ክፍያዎችን፣ ታክሶችን፣ የታክስ ቅነሳዎችን ወይም ማበረታቻዎችን በሥራ ላይ በማዋል ሁኔታዎቹን ማስተካከል ያስፈልጋል፣

ቀ. የሀብት ተጠቃሚ ማኀበረሰቦችንና ግለሰቦች ዘላቂነት ባለው መንገድ አካባቢያቸውንና ሀብቶቻቸውን እንዲያስተዳድሩ (Manage) ድጋፍ የሚሰጡ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፣

በ. ሴቶች በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና አያያዝ ውስጥ ዋና ተዋንያን እንደመሆናቸው ከወንዶች ዕኩል መታየት እና በፓሊሲ፣ በኘሮግራምና በኘሮጀክት ቀየሳ፣ በውሳኔ አሰጣጥና አፈጻጸም ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ የሚያስችላቸው ሥልጣን እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

ተ. በማያቋርጥና ቀጣይ በሆነ መንገድ በመሬትና በተፈጥሮ ሀብት መጠቀምን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ለዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፣

ቸ. ማኀበራዊ ፍትህ፣ በተለይም በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ረገድ፣ ይረጋገጣል፣

ኀ. መደበኛና ትክክለኛ የአካባቢ ሁኔታዎች ግምገማና ክትትል የደረጋል፣ የሚገኘውም መረጃ ለሕዝብ በሰፊው ይሰራጫል፣

ነ. የላቀ የአካባቢና የተፈጥሮ ሀብት ጉዳዮች ግንዛቤና ንቃት በፓሊሲ አውጪዎች፣ በመንግሥት ባለሥልጣኖች እና በሕዝብ ዘንድ እንዲኖር የማበረታታትና፣ እንዲሁም አካባቢን ከሚመለከቱ ጉዳዮች አኳያ "የእንክብካቤ ባህል" ('Conservation Culture") የኀብረተሰቡ የተለያዩ ደረጃዎች እንዲሰርጽ የማደፋፈር እርምጃዎች ይወሰዳሉ፣

ኘ. ቀበሌአዊ፣ ክልላዊና ዓለም አቀፋዊ የአካባቢያዊ መደጋገፍ (Interdependence) ዕውንነት ዕውቅና ያገኛል፣

አ. የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ አያያዝ ተግባሮች በተዋረድ በሁሉም ዘርፎችና በሁሉም ደረጃዎች ይቀናጃሉ፣

ከ. ዝርያዎችና (Species) የተለያዩ ነገዶቻቸው (Varieties) በሕይወት የመቀጠል መብት አላቸው፣ በተጨማሪም ለአሁኑም ሆነ ለመጪዎች ትውልዶች ጠቃሚ ናቸው፣ ወይም ሊሆኑ ይችላሉ፣

ዐ. የእህል ዘሮች፣ የቤት እንስስት፣ ጠቃቅን ሕዋሳት (Micro-organisms) እንዲሁም የዱር ዕፀዋትና እንስሳት የመዋለድ ችሎታ ክቡርና (Invaluable) ሊሸጥ ሊለወጥ የማይችል (Inalienable) ሀብት ስለሆነ በጥንቃቄ ይያዛል፣

ወ. የየዘርፎችና የየመድብለ ዘርፎች የፌዴራል፣ የክልልና የቀበሌ ፓሊሲዎች እና ሥልቶች የተቀናጀ አተገባበር የዚህን የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ዓላማዎች ወደ ግብ ለማድረስ እንደ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ ይታያል።

## 3. የልማት ዘርፎች የአካባቢ ፓሊሲዎች

### 3.1 የአፈር አያያዝና ዘላቂ ግብርና

**ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው:-**

ሀ. ዘላቂ የመሬት አያያዝ ቴክኖሎጂዎች በስፋት እንዳይሠርፁና ተገቢው ሙዓለ ንዋይ እንዳይመደብላቸው የሚገቱ ምክንያቶችን ለማስወገድ ገበሬዎችና እንስሳት

አርቢዎች በመሬትና በተፈጥሮ ሀብር ላይ የተረጋገጠ የማይቋርጥና ቀጣይ የተጠቃሚ ባለመብትነት ስሜት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሁኔታን መፍጠር፣

ለ. ከኢኮኖሚ አኳያ የሚያዋጡ፣ ከአካባቢ አኳያ ጠቀሜታቸው የተረጋገጠ፣ ከስነ ሕይወት አኳያ የማያናውጡና ከአለው አካባቢዎች፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁኔታ አኳያ ሲታዩ ተገቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች እንዲጠሩ፣ እንዲሻሻሉና እንዲሠርፁ በማድረግ የግብርና የምርት ዕድገት የእርሻ ስርዓቶችን የምርት መጨመር ዓቅም ዘላቂነት ባለው መንገድ የሚያጐለብት (Intensify) እንዲሆን ማድረግ፣

ሐ. የአፈር እንክብካቤንና የመሬት አያያዝን ለማሻሻል የአፈርን ውስጣዊ ስብጥርን (Structure) የለምነት ይዘትንና የጥቃቅን ሕዋሳት ሥነ ሕይወትን (Microbiology) የሚያሻሽል የሕያዋን ቅሪት ቁስን (Organic Matter) እና የተፈጥሮ ምግብነት ያላቸው ንጥረ ነገሮችን በተገቢ መንገድ ያዋሀደ አግብኦትን ማራመድ፣

መ. በአዝእርትና በቤት እንስሳት የግብርና ምርት ሂደት ውስጥ የኬሚካላዊና የሕይወት ወለድ ቁሳዊ ማዳበሪያዎችን፣ ቅጠላ ቅጠልን፣ የቤት እንስሳት ፍግንና ብስባሽ /ኮምፓስት/ ጨምሮ፣ መጠናቸው ትክክለኛውን ሚዛን እንዲይዝ በማድረግ የአፈርን ዓለት ወለድና ሥነ ሕይወታዊ ይዘቶችን ጠብቆ በማቆየት ደህንነቱን ማረጋገጥ፣

ሠ. ውጤታማ በሆነ መንገድ መሬትን በዕፀዋት መሸፈን የአፈር መከላትን ለመቆጣጠር እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት መንገዶች አንዱ በመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በመተግበር ላይ ያሉ በርካታ ዘላቂ የእርሻ፣ የእንስሳት ርቢት የደን ልማት ዘዴዎች መሬትን በመደልደልና እርከንን በመሥራት ለተመሠረቱ (Mechanical) የአፈር እንክብካቤ ዘዴዎች አማራጭ መሆናቸውን በመረዳት እንዲስፋፉ የሚያስችል ሁኔታ መፍጥር፣

ረ. ከአፈር እንክብካቤ ተግባር ባላነሰ ሁኔታ ለሕይወት ወለድ ቁስ ክምችትና ለእዝዕርት ምርት መሠመር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስለሚያደርግ ድርቅ በሚያጠቃቸውና አነስተኛ ዝናብ በሚያገኙ አካባቢዎች ለውሃ የሚያደረገውን እንክብካቤ ማበረታታት፣

ሰ. ወጪን ከመቀነስና ተቀባይነትን ከማረጋገጥ አንፃር የመሬት እንክብካቤን ማሻሻል አሁን ካሉት የአያያዝ ሥርዓቶች፣ ቴክኖሎጂዎችን ዕውቀት ጋር የተገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሸ. የኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች የተለያየ የአካባቢ ሁኔታ ያላቸው ከመሆናቸው አንፃር የግብርና ምርምርና የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ለእርሻና ለመሬት አጠቃቀም ሥርዓቶች ልዩነቶች የላቀ ትኩረት እንዲሰጡና ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ የመሬት አያያዝ ሥርዓቶች እንዲሰጡና ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ የመሬት አያያዝ ሥርዓቶች እንዲጠናከሩ የድጋፍ ቅድሚያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማረጋገጥ፣

ቀ. አንፃራዊ የሆኑ አካባቢያዊ አንድ ወጥነት ላላቸው የኢትዮጵያ ቆላማ ቦታዎች ተገቢ የሆኑ ከፍተኛ የምርት ውጤቶችን የሚሰጡ የአርሻ ሥራና የመሬት አያያዝ ሥርዓቶችን ለመዘርጋት የሚያስችሉ የረዥም ጊዜ የግብርና ምርምር መርሐ ግብሮችን ማስፋፋት፣

በ. የግብርና ልማት ዕቅድ፣ በኢኮኖሚያዊ የወጪና ጥቅም ንፅፅር ስሌት ትንታኔ (Economic cost-benefit analysis) ውስጥ፣ በአፈር መከላት፣ በመሬት ጨዋማ መሆንና በአፈርና በውሃ መበከል ምክንያቶች ሊደርሱ የሚችሉትን ወጪዎች (Cost) ማካታቱን ማረጋገጥ፣

ተ. የግብርና ግብዐቶች፣ በአፈሩ ዐለት ወለድ ቁስና በጥቃቅን ሕዋሳት ሥነ ሕይወት ላይ (Microbiology) ከረዥም ጊዜ በኃላ ጊዜ በኃላ ጉዳት በሚያስከትል ዘላቂ ባልሆነ የአስፈላጊ ንጥረ ነገሮች አቅርቦት ላይ ከሚያተኩሩ ይልቅ፣ እንደ አፈሩ ዓለት ወለድ ቁሳዊ፣ ኬሚካላዊና ስነ ህይወታዊ ክፍሎች ስብጥር ፍላጎት፣ የተለያዩና ተደጋጋፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ቸ. የግጦሽ መሬቶች እንደገና እንዲያቆጠቁጡና የአፈር መከላት እንዲቀንስ ለማበረታታት፣ ጭድን፣ በእርሻ ቦታ የተመረተ የእንስሳት መኖንና የሣር ድርቆሽን እንዲሁም ከግጦሽ መስኮችና ከኰረብታማ ቦታዎች የሚገኝ ሣርንና ሌሎች እንስሳት ምግብነት ያላቸውን ቅጠላ ቅጠሎችን በማጨድ ወይም በመቁረጥ ተሸክሞ ወደ በረት በመውሰድ የቤት እንስሳትን በበረት ውስጥ አስሮ የመመገብ አሠራር (Stall feeding) መጀመር፣

ኀ. የማገዶ፣ የቤትና የመሳሪያዎች መሥሪያ፣ የእንስሳት መኖና የሌሎች የዛፍ ውጤቶችን መጠን እንዲጨምር፣ በእርሻ ቦታ፣ በገበሬ መኖሪያ ቤት ዙሪያና አፈራቸው እየተከላ ባሉ ወይም በተከላባቸው ኮረብታዎች ላይ የደን ተከላን ማስፋፋት፣

ነ. ለተለያዩ የአካባቢ ሁኔታዎች ተስማሚነትን ለማረጋገጥ በቀላሉ የመለወጥ ጠባይንና ተባዮችንና በሽታዎችን የመቋቋም ችሎታን ለማጎልበት፣ በዝርያ ልማት (Breeding) ውስጥ በአንድ ወጥ የዕፅዋትና የእንስሳት ዝርያዎች (Single Line Plant Varieties and Animal Breeds) ላይ በመስጠት ላይ ያለው ትኩረት በተቻለ መጠን ተደጋጋፊና ተስማሚ ወደ ሆኑ ወደ ተለያዩ ዝርያዎች ቅንጅት እንዲለወጥ ማድረግ፣

ኘ. ከኬሚካላዊ ቁጥጥር ይልቅ የስነ ሕይዎታዊንና የባህላዊ ዘዴዎች እንዲሁም ተባይንና በሽታን ለመቋቋም በሚችሉ የእዝርዕት ዓይነቶች፣ የፌርሞኖችን ወይም የመካን ወንድ የተሓዋስያን ቁጥጥርን (Sterol male Techniques)፣ ወደ አቀናጀ ተባይንና በሽታን የመመከት፣ ዘዴ ማድላት፣

አ. የግብርና ግብአት ኬሚካሎችን አጠቃቀም ደንብ ለማስያዝ ብቃት ያላቸው ህግጋትን በማውጣት የህዝብንና የአካባቢን ጤንነት መጠበቅ፣

ከ. የተፈጥሮ ሀብትንና የአካባቢን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሲሰጡ ሊያደርሱ የሚችሏቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎች በአኗኗር ዘይቤ ላይ የሚያመጡት ለውጥ በደንብ እንዲጠናና የቅድመ ጥንቃቄ መሠረተ ሀሳብ በሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ በተለይም ይህ ጥንቃቄ ዕውቀታችን በጣም ዝቅተኛ በሆነበት በከብት አርቢው ቆላማ አካባቢ ላይ መወሰዱን ማረጋገጥ፣

ወ. አዳዲስ ቴክኒካዊ የማሻሻያ ሃሳቦች፣ አሁን ካሉት የእንስሳት ርቢና የግብርና ሥርዓቶች፣ የግብርና ስርዓተ መሕድራዊ ሁኔታዎችና ጐልተው ከሚታዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ዐ. በኢትዮጵያ ውስጥ በሰፋፊ የግጦሽ መሬቶች ላይ በሚገኙት የመስኖ ሥራዎች ሁሉ የአካባቢ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ተፅዕኖ ግምገማ ማካሄድና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአካባቢ፣ በማኅበራዊ ሁኔታና በኢኮኖሚ ላይ ያስከትሏቸውን አሉታዊ ውጤቶች ለማስተካከል የሚያስችል መርሐ ግብር መዘርጋት።

### 3.2 የደንና የዛፍ ሀብት

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ማኅበረሰቦች፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚና መንግሥት በደን ልማት ተደጋጋፊ የሆኑ ሚናዋች ያሏቸው መሆኑን መገንዘብ፣

ለ. ዘላቂነትን ለማረጋገጥ፣ ወጪን ለመቀነስና ግጭትን በቅድሚያ ለማስወገድ፣ የሚመለከታቸው ግለሰቦች፣ ማኅበረሰቦችና እንዲሁም መንግሥት የደን ልማት መርሐ ግብሮችን በማቀድና በመተግበር ረገድ በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት፣

ሐ. የደን ልማት ሥልቶች፣ የደን ሀብቶች ልማት፣ አያያዝና እንክብካቤ፣ ከመሬትና ከውሃ ሀብቶች፣ ከኃይል ምንጭ ሀብቶች፣ ከሥርዓተ መሕድሮችና ከጄኔቲክ ሀብቶች እንዲሁም ከአዝዕርትና ከቤት እንስሳት ከቤት እንስሳት ግብርና ጋር መቀናጀታቸውን ማረጋጥ፣

መ. በውጭ ዝራያዎች ደን የማልማት ተግባሮች በጎሮ፣ በከተሞች ዙሪያና ለተወሰኑ የኢንዱስትሪና ለሌሎች ፕሮጀክቶች አገለግሎት የተወሰኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ። በውጭ ዝሪያዎች ላይ አስተማማኝ መረጃና ዕውቀት እስኪኖረን ድረስ ከዚህ ውጭ የሆነውን የደን ልማት ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑና የአካባቢውን ደህንነት የሚያረጋግጡ በመሆናቸው በቦታው ነባር ዝርያዎች ማካሄድ፣

ሠ. ሊታረሱ በማይችሉ ሥፋራዎች የደን መንሰራራትን የተፈጥሮ ሂደት ለማገዝ ግጦሽና ዛፍ ቆረጣን መከልከል፣ አስፈላጊ የቦታው ነባር ዝርያዎችን መርጦ መትከልና አቅም በፈቀደ መጠን ሌሎች የማመቻቸት ተግባሮችን ማካሄድ፣

ረ. "ዘላቂ የደን አያያዝ" ("Sustainable forest management") ዕውን የሚሆነው ማኅበራዊ ተቀባይነትና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ሲኖርና በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተቆርጦ የሚሰበሰበው እንጨት ደኑ በተፈጥሮ ዕድገቱ ሊሰጥ ከሚችለው ምርት ጋር ሲመጣጠን ነው የሚለውን መርህ ማክበር፣

ሰ. በቀላሉ ሊጐዱ በሚችሉ የደን መሬቶችና ሥርዓተ መሕድሮች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና የሚቀንሱ የግብርናና ሌሎች ፓሊሲዎችንና መርሐ ግብሮችን ማራመድ፣

ሸ. እንስሳት በጥብቅ የደን ቦታዎች ውስጥ በግጦሽ እንዳይሰማሩ የሚከለክሉ የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ሥርዓቶችን ማራመድ፣

ቀ. በደን ላይ ያለውን ጫና ለመቀነስ አቅምና ሁኔታ በፈቀደ መጠን ለግንባታና ለማገዶ የእንጨት ምትክ የሚሆኑ አማራጮ እንዲኖሩ ማድረግ፣

### 3.3. የጄኔቴክ፣ የዝሪያዎችና የስነ መሕድር ብዝሀ ህይወት

**ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-**

ሀ. የሥፍራ ውስጥ እንክብካቤ ሥርዓቶችን (Insitu Conservation System) (ማለትም በጥብቅ የተፈጥሮ ቦታዎች፣ በገበሬ ማሳዎች ወዘተ) ማራመድ ለማዳና ለማዳ ላልሆነ ብዝሀ ህይወት እንክብካቤ ተቀዳሚ ግብ እንዲሆን ማበረታታት፣ በተደራቢነትም ከሥፍራ ውጭ እንክብካቤ ሥርዓቶችን (Exsitu Conservation Systems) በጂን ባንኮች፣ በእርሻዎች፣ በዓፀዶች (Botanical Gardens) በእንስሳት ርቢ የግጦሽ ቦታዎች፣ በአብያተ እንስሳት (Zoos) የሚደረግ እንክብካቤን ማበረታታት፣

ተ. አንዳንድ የአንሰሳትና የዕፀዋት ዝርያዎች ለሰዎችና እንዲሁም ለሌሎች እንስሳትና ዕፀዋት ቀበኛ ወይም ተባይ መሆናቸውን ወይም ለሰዎች፣ ለአዝርዕት ለቤት እንስሳት ለበሽታ ምንጭ ሊሆኑ መቻላቸውን ማወቅና መቆጣጠር።

### 3.4 የውኃ ሀብት

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው

ሀ. የአካባቢ የጤና ጠንቆችን መቆጣጠር ለግድቦችና ለመስኖ ሥርዓቶች ንድፍ፣ ግንባታና በጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ. የተፈጥሮ ሥርዓተ መሕድሮች፣ በተለይ ረግረጎችና ወንዞች በሚመጡባቸው ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙ ደኖች፣ የውሃን ጥራትና መጠን የሚወስኑ መሠረቶች ስለሆኑ እነርሱን የመንከባከብና ከተጐሳቆሉም እንዲያገግሙ የማገዝ ተግባርን ከውሃ ሀብቶች እንክብካቤ፣ ልማትና አያያዝ ጋር የማቀናጀት አስፈላጊነትን መገንዘብ፣

ሐ. ከውጭ የሚመጡ ዝርያዎችን ወደ ውሃ ሥርዓተ መሕድሮች ለማስገባት የሚቀርብ ማንኛውም ሃሳብ የሚተገበረው ዝርዝር ስነ መሕድራዊ ምርምር ከተካሄደበትና ከአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ካለፈ በኃላ መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ. ውሃና የብስ የሚገናኙባቸው ሥፍራዎች (Interface between Water Bodies and Land) መጠበቃቸውን ማረጋገጥ/ ለምሳሌ፣ የሐይቅ ደርቻዎች፣ የወንዝ ዳርቻዎች እና ረግረጎች/

ሠ. አብዛኛዎቹ በከፍተኛና በመካከለኛ ደረጃ በመስኖ ሊለሙ የሚችሉ ቦታዎች የሚገኙት በእንስሳት አርቢዎች በተያዙ የቆላ ሰፋፊ የግጦሽ ቦታዎች እንደመሆኑ መጠን የእንስሳት አርቢዎች የደረቅ ወቅት ግጦሽ መሬት በእርሻ ቢያዝ በእንስሳት እርባታ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት የሚያመዛዝን ስሌት (opportunity Cost በሁሉም የመስኖ ፕሮጀክቶች የወጪና የጥቅም ማነፃፀሪያ ትንተና (Cost-Benefit Analysis) ውስጥ እንዲካተት ማድረግ፣

ረ. የሥነ መሕድራዊ ሚዛን እንዳይዛባ ለማድረግ እንዲቻል የውሃ ፓሊሲዎች፣ መርሐ ግብሮችና ፕሮጀክቶች ሲታቀዱ፣ ሲነደፉና ተግባራዊ ሲደረጉ በሚነካው ቀበሌ የሚኖሩ የውሃ ሀብት ተጠቃሚዎች፣ በተለይም ሴቶችና እንሰሳት ጠባቂዎች፣ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

ሰ. ዐበይት የሆኑ የውሃ እንክብካቤ፣ ልማትና አያያዝ ፕሮጀክቶች ሁሉ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ ማድረግ፣ እንዲሁም በተፋሰሶች ለሚገኙ ደኖች፣ ረግረጎችና ሌሎች አግባብነት ላላቸው ቁልፍ ስርዐተ መሕድሮች የሚደረግ እንክብካቤ ሊያስከትል የሚችለው ወጭና ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም በፕሮጀክቶቹ የኢኮኖሚ ትንተና ውስጥ እንዲካከተት ማድረግ፣

ሸ. ፕሮጀክቶች በሚካሄድበት ቦታ ላይ ሥልጥና በመስጠትና በማሳ ደረጃ ውጤታማ የውሃ አያያዝ ስልቶች እንዲኖናሩ በማበረታታት መካከለኛና ትላልቅ የመስኖ ሥራዎች የተሻለ ውጤት እንዲያስገኙ የሚያደርግ ሁኔታ መፍጠር፣

ቀ. የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ውሃ መጠንን የማጐልበት ድጋፍ ሊሠጡ የሚችሉ አዋጭ የሆኑ የውሃ መጠን ማበልፀጊያ ተግባሮች አቅም በፈቀደ መጠን እንዲበረታቱ ማድረግ፣

በ. ለአገልግሎት የዋለ ውሃ /ፍሳሽ/ በአካባቢ ወይም በጤና ላይ ጠንቅ ከማምጣት ነፃ መሆኑን በማረጋገጥ ወይም ብዙ ወጭ ሳያስከትል ከነዚህ ጠንቆች ነፃ እንዲሆን በማድረግ ደጋግሞ መጠቀም (Recycle)፡፡

### 3.5 የኃይል ምንጭ

ፖሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የኃይል ልማትን ከኃይል ቁጠባ፣ ከአካባቢ ጥበቃና ከታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች ዘላቂ አጠቃቀም ጋር የሚያቀናጅ መድብለ ዘርፋዊ (Inter-sectoral) የዕቅድና የልማት ሂደትን መከተል፣

ለ. ዘላቂነትን፣ የአካባቢ ጥበቃና የኃይል ምንጮች ቀጣይነትን ለማረጋገጥ፣ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ማልማትና የፎሲል ኃይል ምንጭ (Fossil Energy Sources) አጠቃቀም እየቀነሰ እንዲሄድ ማድረግ፣

ሐ. በከፍተኛ የማገዶ እንጨት ተጠቃሚ የሆኑ ተቋሞችና እንዱስትሪዎች የራሳቸውን የማገዶ እንጨት ተክል እንዲያቋቁሙ ወይም ከማገዶ እንጨት ተክሎች ባለሀብቶች ጋር ውል በመመሰርት ፍላጐታቸውን እንዲያሟሉ ማድረግ፣

መ. የግል ባለሀብቶች በከተሞች አካባቢ የማገዶ ተክል እንዲያቋቁሙ ለማስቻል መንግስት መሬት የሚያከራይበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

ሠ. ለማኀበረሰቡና በአጠቃላይም ለአገሪቱ ጥቅምን የሚጨምር እና በተፈጥሮ ሀብቶች መሠረት ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት የሚያስወግድ ወይም ቢያንስ ልዩነት ወደ ማያመጣበት ደረጃ የሚቀንስ የበሰለ የውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር፣ የውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎችን እና ሌሎች ትላልቅ የኃይል ማመንጫ ተቋሞችን የሚመለከቱ ጥናቶች ጠበቅ ያለ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ማካተታቸውን ማረጋገጥ፣

ረ. የማኀበረሰቦችን የኃይል ፍላጎቶች በተሻለ መንገድ ለማሟላትና ለግልና ለማኀበረሰብ ዘርፎች አካባቢን የማይበክሉ የኃይል ምንጮች የማልማትና ወደ ገበያ የማቅረብ ዕድል ከፍ ለማድረግ በኃይል ዘርፉ የሚያገለግሉትን የመዋቅር የዋጋና የቁጥጥር ሁኔታዎችን መመርመርና የማሻሻያ ሃሳቦችን መጠቆም፣

ሰ. የውሃ ሀብት የኢትዮጵያ የሃይል ፍላጐት ለማሟላት ከፍተኛ ድርሻ ያለው መሆንና ሀይል በማመንጨቱ በአካባቢ ላይ ብክለት የማያደርስ መሆኑን መገንዘብ፣

ሸ. በእያንዳንዱ የገበሬ መኖሪያ የእንጨት ፍላጎትን ለማርካት የሚያስችል የዛፍ ተክላ መካሄዱን ለማረጋገጥ የኤክስቴንሽን መርሐ ግብሮች በእርሻ ማሳዎችና በገበሬ ቤቶች ዙሪያ ዛፍ መትከል ላይ እንዲያተኩሩ ማድርግ፣

ቀ. ከሕይዋን ቁስ (Biomass) የሚገኝ ኢነርጂን ለመተካት የሚችሉ የኃይል ምንጮችንና ቴክኖለጂዎችን ፈልጎ ማግኘት፣ ማልማትና ከሁኔታዎች ጋር አስማምቶ በጥቅም ላይ ማዋል፡፡

### 3.6 የማዕድን ሀብቶች

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የማዕድን ሀብቶች አልቀው መሟጠጣቸው ስለማይቀር፣ ማዕድን በሚወጣበት ወቅትና ከዚህም በኃላ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በመውሰድ መሬቱን ለግብርናና ለሌሎች የኢኮኖሚ ተግባሮች ለማዋል የሚችል የረዥም ጊዜ የመሬቱ አጠቃቀም ሁኔታ በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣

ለ. የመሬትንና የሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ከአካባቢ ሕጎችና ደንቦች ጋር እንዲጣጣም ሆኖ የተደራጀና ኃላፊነት የሚሰማው የማዕድን ቁፋሮ ተግባርን እንዲያከናውኑ ለእጅ ባለሙያዎችና ለአነስተኛ ማዕድን አውጪዎች ድጋፍ መስጠትና ማበረታታት፣

ሐ. ማዕድን አውጪ ማኀበረሰቦችን ስለ አካባቢ ጥበቃና የቀድሞ የማዕድን ሥፍራዎች ተሀድሶ ስለሚያገኙበት መንገድ መምከርና ማሰልጠን፣

መ. እየጨመረ ከመጣው የግሉ ዘርፍ ሚናና ወደፊትም በከፍተኛ የማዕድን ልማት ሥራዎች ውስጥ የውጭ ኢንቨስትመንት ሊኖር ከመቻሉ አንፃር፣ የመንግሥት የማዕድን መሥሪያ ቤቶችን የአካባቢ ጥበቃን የመቆጣጠርና የማስተዳዳር አቅም ማጠናከር፣

ሠ. የማዕድን ማውጣት ተግባር በሚከናወንበት ወቅት ስለአካባቢ አያያዝ የቴክኒክ ምክርና ዕርዳታ መስጠት፣ እንዲሁም ሁኔታ ክትትል (monitoring) እና የሕዝብና የኢንዱስትሪ ሠራተኞች የአካባቢ ትምህርት መርሐ ግብሮችን መዘርጋት፣

ረ. የአካባቢ ጥበቃንና የሥራ ውጤት ቅልጥፍናን ለማሻሻል ለእጅ ባለሙያ የማዕድን አውጪዎች የቴክኒክና የማቴሪያል ዕርዳታ መስጠት፣

ሰ. ማዕድን አውጪዎች የቅድመ ልማት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት እንዲዘጋጁ፣ የማዕድን ሥራ በሚካሄድበት ወቅት አስተማማኝ የሆነ የአካባቢ አያያዝ እንዲኖር፣ እንዲሁም የማዕድን ሥራ በሚካሄድበት ወቅትና ከዚያም በኃላ በተገቢው መንገድ በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት የሚቀንሱና የሚያስተካክሉ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማድረግ እንዲቻል በውል ገደቦች መጠቀም፣

ሸ. ማዕድን የማውጣት ተግባር በሚመለከት ግልጽና ዝርዝር የሆኑ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን አውጥቶ በተግባር ላይ ማዋል፣

ቀ. የማዕድን ማውጣት ተግባራት በመካሄዳቸው ምክንያት የሚከሰተውን የለም አፈር መወገድና የዕፀዋት ሽፋን መጥፋት ተስተካክሎ ቦታው እንደገና ለምርት አገልግሎት እንዲውል ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፡፡

### 3.7 የከተሞች አካባቢና የአካባቢ ጤና

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት በሚያመጣው የከተሞች መበራከትና መስፋት ሳቢያ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን፣ የሕዝብ ሠፈራን እና የአካባቢ ጤናን የሚመለከቱ ጉዳዮች በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ በሚካሄዱ የዕቅድና የልማት ተግባሮች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ፣

ለ. የተፈጥሮ ስርዓተ መሕድሮችን ጠብቆ ለማቆየት እንዲቻል በከተሞች ልማትና አያያዝ የዕድ ውስጥ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮአዊ ገፅታዎችን በተጣጣመ መንገድ ማቀናጀት፣

ሐ. ዘላቂ የሆነ የከተማ ልማትን ለማምጣት የተሻሻለ የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ በፌዴራል በክልል አጀንዳዎች ላይ ከፍተኛውን ቦታ እንዲይዝ ማድረግ፣

መ. እያንዳንዱ ቤተሰብ የራሱን ቤት እንዲሠራ ማበረታታት እንዲሁም እያንዳንዱ ማህበረሰብና ቤተሰብ በአስተማማኝና በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቅሶ ሠፈሩን ለማሻሻልና የሰውና የመኖሪያ ቤት ቆሻሻ ማስወገጃዎችን እንዲያዘጋጅ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር መርዳት፣

ሠ. ከፍላጎት የሚመነጩና በማህብረሰቦች የሚመሩ የከተሞች አካባቢ ማሻሻያ መርሐ ግብሮች፣ እንዲሁም የንፅህና መገልገያዎች ዘላቂ አጠቃቀምና የእንክብካቤ ተግባራት እንዲስፋፉ የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ችግሮችን በተመለከተ በሚካሄዱ የትምህርትና የግንዛቤ መርሐ ግብሮች አማካኝነት የአመለካከት ለውጥ እንዲገኝ ማድረግ፣ ወሳኝ መሆኑን ማወቅና ይህንኑ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት እገዛ ማድረግ፣

ረ. የተቀናጀ የንፅህና አገልግሎትን በማስፋፋት ተግባር በመንግሥትና በማህበረሰቦች መካከል የሥራ ድግግፍ እንዲኖርና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተጨማሪ ሚናም እንዲታከልበት ማድረግ፣

ሰ. የመኖሪያ ቤቶች አሠራርና የንፅህና አጠባበቅ ቴክኖጃዎችና የመቆጣጠሪያ ደረጃዎች (Standards) ከተጠቃሚዎች አቅምና የመክፈል ችሎታ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውንና በከተሞች ከሚገኙ በጣም የተለያዩ ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የበሽታ ተዛማችነት (Epidemiological)፣ የአየር ንብረትና የቦታ አቀማመጥ ሁኔታዎች ጋር የተጣጠሙና እንደሁኔታዎች ሊሻሻሉ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ሸ. ለቆሻሻ የማጠራቀምና በአስተማማኝ ዘዴ የማስወገድ አገልግሎት ቅድሚያ መስጠት፣

ቀ. በአንድ በኩል ዘላቂና ጤናማ የከተማ አካባቢ ለማስገኘት በቂ የውሃ አቅርቦት አስፈላጊ መሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጤና አጠባበቅ ቴክኖጂዎች ምርጫ በሚደረግበት ወቅት የውሃ ፍጆታን መቀነስ መቻል እንደ ዋና መለኪያ ነጥብ መወሰድ እንዳለበት መገንዘብ፣

በ. በአዲስ አበባና በሌሎች ነባር ከተሞች ውስጥ ገቢው ዝቅተኛ የሆነ ብዙ ነዋሪ ባላቸው በተጨናነቁ ሠፈሮች ሽታ ማስወገጃ ያላቸው የተሻሻሉ የወል የመፀዳጃ ቤቶችን (VIP-Ventilated Improved Pit Latrines) መገንባትና በፅዳት መኪና በየጊዜው እንዲመጠጡ ማድረግ፣ ይኸም ከትምህርት፣ ከጤናና ከንፅህና ሣይንስ (hygiene) መርሐ ግብሮች ጋር ተቀናጅቶና የፅድሳትና የፅዳት ክትትልና የጐርፍ ውሃ (Storm Water) ማስወገድ ታክሎበት፣ ሰፉ ያለ የከተሞች ማሻሻያ መርሐ ግብር አፈፃፀም አካል በመሆን በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣

ተ. ቁጥሩ አነስ ያለ ሕዝብ በሠፈረባቸው ከተሞች ዙሪያ የቤት ሥራ ፈቃድ ሲሰጥ የቤተሰብ መፀዳጀ ቤት መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ግዴታ እንዲኖርና ከጤናና ከጤና ሳይንስ ግንዛቤ መርሐ ግብሮች ጋር እንዲዋሀድ ማድረግ፣

ቸ. ቤተሰቦች፣ የቤት ሥራ ማህበራትና ማህበረሰቦች መፀዳጃ ቤቶችን እንዲሰሩ እንዲሁም የግል ድርጅቶች የመፀዳጃ ቤቶችን የማፅዳት፣ ቆሻሻ የመስብሰብና የማስወገድ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የሚያስችሏቸው ሁኔታዎችን መፍጠር፣

ኀ. በኢትዮጵያ ትላልቅ ከተሞች ተስማሚ የሆኑ የደረቅ ቆሻሻ መዳፊያና መቅበሪያ ቦታዎችን (Sanitary Landfill Sites) ለማመልከት የሚያስችሉ ጥናቶችን ማካሄድ፣

ነ. ለመዝናኛ፣ ለዓፅዋትና ለእንስሳት መጠለያና ለአየር ንብረት ማሻሻያ እንዲሆኑ በከተሞች ውስጥ ለምለም ቦታዎችን በዕቅድ ማዘጋጀትና የማህበረሰብ ደኖችንና የማገዶ እንጨት ጫካዎችን ማልማት፣

ኘ. በከተሞች፣ በተለይም በትላልቆቹ፣ የቱቦ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎችና የፍሳሽ ማጣሪያ መገልገያዎች እንዲሰሩ ማበረታታት፣

አ. ከመኖሪያ ቤቶችና ከድርጅቶች የሚወጡ ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻዎች በተቻለ መጠን ለኃይል ምንጭ፣ ለማዳበሪያና ለሌላ ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ።

## 3.8 ከኢንዱስትሪ ከሚወጣ ቆሻሻና ከአደገኛ ንጥረ ነገሮች የሚመነጭ ብክለት

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ከኢንዱስትሪ ተቋሞችና ከግለሰብ ወይም ከማኀበረሰብ የመገልገያ ዕቃዎች ወይም ከማናቸውም ምንጮች የሚለቀቁ ሊጐዱ የሚችሉ ንጥረ ነገሮችን፣ ህይወት ያላቸው ነገሮችን ወይም ቅሪቶቻቸውን የመቀነስ ወይም ሲቻል የማቆም፣ በጣም ጐጂ የሆኑትን ንጥረ ነገሮች ደግሞ መልቀቅ እንዳይፈቀድ የማድረግ የቅድመ ጥንቃቄ መሠረተ ሀሳብን መከተል፣

ለ. ብክለትን እንደየ ሁኔታው የመከልከል በተለይም በጣም ጐጂ የሆኑ ነገሮች እንዳይለቀቁ የማድረግ የቅድመ ጠንቃቄ መሠረተ ሀሳብ እንደተጠበቀ ሆኖ ብክለት በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ስለሚችል፣ «በካዩ መክፈል አለበት» («The Polluter Pays») የሚለውን መርህ መቀበልና ብክለትን የሚያደርሱ ተቋሞች፣ ማዘጋጀ

ቤቶች እና የወረዳ ምክር ቤቶች የራሳቸው የሆኑ ተገቢ የብክለት ማስወገጃ አገልግሎቶች እንዲኖሩዋቸው ማድረግ፣

ሐ. ብክለትን በመቆጣጠርና በውሃ ሀብት፣ በግብርና፣ በሠፈራ፣ በጤናና በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፓሊሲዎች መካከል ግልጽ የሆኑ ትስስሮች እንዲፈጠሩ ማድረግ፣

መ. ብቁ የሆነ የግብርና (የአዝዕርትና የቤት እንስሳት) ኬሚካሎች እና የጥቃቅን ሕዋሳት አጠቃቀም ደንብ እንዲኖር ማድረግ፣

ሠ. የብክለት ቁጥጥር ተግባር ከበካዩ ቁስ አደገኛነትና ሳይለወጥ የመቆየት፣ የመጨመር ወይም የመራባት ችሎታ ጋር የተመጣጠነ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ. በውሃ ጉድጎዶች እና በግድቦች አጠገብ የሚዘጋጁ የፍሳሽ መድፊያና መቅበሪያ ቦታዎች ሊኖራቸው የሚገባውን የርቀት መጠን የሚወሰኑና ርቀቱ መጠበቁን የሚያረጋግጡ ደንቦችን ማውጣት፣

ሰ. ቆሻሻ ማስወገድንና የህዝብና የኢንዱስትሪ ንፅሕናን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣት፣ በሕግ የተወሰኑ የቁጥጥር ደረጃዎችን በተመጣጣኝ ወጭ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎችን መዘርጋትና በተግባር እንዲውሉ የሚያስችሉ ደንቦችን ማውጣት፣

ሸ. ከህክምና ከግብርናና ከሌሎችም አደገኛ ሊሆኑ በሚችሉ ሕይዋንና በቅሪቶቻቸው እንዲሁም በንጥረ ነገሮች ከሚጠቀሙ ዘርፎች የሚመነጩ ብክለቶች አያያዝንና ማስወገድን የሚመለከት አገር አቀፍ ሥልትና ሥልቱን ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ማውጣት፣

ቀ. ጠንቀኛና አደገኛ የሆኑ ነገሮች አያያዝንና አከመቻቸትን፣ ማዕድን ማውጣትን፣ የሕዝብና የኢንዱስትሪ ንፅሕናን፣ ቆሻሻ ማስወገድንና የውሃ ጥራትን በተመለከተ የመሬት፣ የአየርና የውሃ ብክለት ቁጥጥር ደረጃዎችን ለመቃኘትና መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣

በ. መርዛማ፣ ጠንቀኛና ሬዲዮአክቲቭ (Radioactive Substances) የሆኑ ነገሮችን ዝርዝር የያዘ ወቅታዊ መዝገብ እንዲኖር ማድረግና መረጃው በተጠየቀ ጊዜ መስጠት፣

ተ. የኢንዱስትሪና የማዕድን ማውጣት ተግባራትን ጨምሮ ሁሉም የመንግሥትና የግል የልማት እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ አንፃር አስተማማኝ የሆኑ አሠራሮችን

መያዛቸውን ለማረጋገጥ የአካባቢ (Audit) ኦዲት ምርመራዎችን በየወቅቱ ማካሄድ፣

ቸ. የምግቦች፣ የመድሃኒቶች፣ የማስዋቢያዎችና (Cosmetics) እንዲሁም የሌሎች ኬሚካሎች ምንነት፣ አጠቃቀምንና ከጥቅም ውጭ የሚሆኑበት ዕለትን አሟልቶ የሚዘረዝር፣ እንዲሁም ይዘቱ መርዛማ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ አደገኛ የሆነ ኬሚካል ካለበት ሁኔታውን በግልፅና በጉልህ የሚያሳይ ምልክት እንዲለጠፍ ማስገደድ፣

ቀ. በአንድ በኩል ዘላቂና ጤናማ የከተማ አካባቢ ለማስገኘት በቂ የውሃ አቅርቦት አስፈላጊ መሆኑን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጤና አጠባበቅ ቴክኖሎጆዎች ምርጫ በሚደረግበት ወቅት የውሃ ፍጆታን መቀነስ መቻል እንደ ዋና መለኪያ ነጥብ መወሰድ እንዳለበት መገንዘብ፣

በ. በአዲስ አበባና በሌሎች ነባር ከተሞች ውስጥ ገቢው ዝቅተኛ የሆነ ብዙ ነዋሪ ባላቸው በተጨናነቁ ሠፈሮች ሽታ ማስወገጃ ያላቸው የተሻሻሉ የወል የመፀዳጃ ቤቶችን (VIP-Ventilated Improved Pit Latrines) መገንባትና በዕዳት መኪና በየጊዜው እንዲመጠጡ ማድረግ፣ ይኸም ከትምህርት፣ ከጤናና ከንፅህና ሣይንስ (Hygiene) መርሐ ግብሮች ጋር ተቀናጅቶና የዕድሳትና የፅዳት ክትትልና የጐርፍ ውሃ (Storm Water) ማስወገድ ታክሎበት፣ ሰፋ ያለ የከተሞች ማሻሻያ መርሐ ግብር አፈፃፀም አካል በመሆን በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣

ተ. ቁጥር አነስ ያለ ሕዝብ በሠፈረባቸው ከተሞችና በከተሞች ዙሪያ የቤት ሥራ ፈቃድ ሲሰጥ የቤተሰብ መፀዳጃ ቤት መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ግዴታ እንዲኖርና ከጤናና ከጤና ሳይንስ ግንዛቤ መርሐ ግብሮች ጋር እንዲዋሀድ ማድረግ፣

ቸ. ቤተሰቦች፣ የቤት ሥራ ማህበራትና ማህበረሰቦች መፀደጃ ቤቶችን እንዲሰሩ እንዲሁም የግል ድርጅቶች የመፀዳጃ ቤቶችን የማፅዳት፣ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማስወገድ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የሚያስችሏቸው ሁኔታዎችን መፍጠር፣

ነ. በኢትዮጵያ ትላልቅ ከተሞች ተስማሚ የሆኑ የደረቅ ቆሻሻ መድፊያና መቅበሪያ ቦታዎችን (Sanitary Landfill sites) ለማመልከት የሚያስችሉ ጥናቶችን ማካሄድ፣

ነ. ለመዝናኛ፣ ለዕፅዋትና ለእንስሰት መጠለያ ለአየር ንብረት ማሻሻያ እንዲሆኑ በከተሞች ውስጥ ለምለም ቦታዎችን (Green Spaces) በዕቅድ ማዘጋጀትና የማህበረሰብ ደኖችንና የማገዶ እንጨት ጫካዎችን ማልማት፣

ኘ. በከተሞች፣ በተለይም በትላልቆቹ፣ የቱቦ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎችና የፍሳሽ ማጣሪያ መገልገያዎች እንዲሰሩ ማበረታታት፣

አ. ከመኖሪያ ቤቶችና ከድርጅቶች የሚወጡ ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻዎች በተቻለ መጠን ለኃይል ምንጭ፣ ለማዳበሪያና ለሌላ ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ።

## 3.9 የአየር ብክለት የአየር ንብረት ለውጥ

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. አገሪቷ በአየር ንብረት መለዋወጥ በከፍተኛ ደረጃ የምትጠቃ ስለሆነ፣ የአየር ንብረት የክትትል መርሐ ግብር እንዲዘረጋ አመቺ ሁኔታ መፍጠር፣

ለ. በአየር ውስጥ ላሉት ሙቀት ሳቢ ጋዞች (Green House Gases) መጨመር ሀገሪቱ የምታደርገው አስተዋፅኦ በጣም አነስተኛ ቢሆንም የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም በሚመለከት የማያወላውል አም እንዲኖራት አስፈላጊ ነው፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድም በከፍተኛ መጠን ሙቀት ሳቢ ገዞችን የሚያመርቱ አገሮች የአየር ንብረት ለውጡን እንዲቋቋሙ ለመገፋፋት የሚያስችል የሞራል አቋም መሆኑን መረዳት፣

ሐ. ኢትዮጵያ በካይ ጋዞችን በጉላ መጠን ከማያወጡ ከውሃ፣ ከከርሰ ምድር ሙቀትና ከፀሐይ ጨረር ኃይልን በማመንጨት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ከፍተኛ ዕምቅ ኃይል ስለአላት የአካባቢና የኢኮኖሚ ልማት ፍላጐቿች እና ወደፊት ኃይልን ለማልማት ያላት ምቹ ሁኔታ ወደ አየር ውስጥ የሚገቡ ሙቀት ሳቢ ጋዞችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመቀነስ ካላት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆኑን መገንዘብ፣

መ. የኢትዮጵያ ደጋማው ክፍል የሳሳ መካች የአየር ሽፋን (Protective Atmosphere) ስለአለውና፣ በዚህም የተነሳ ለአልትራቫዮሌት ጨረሮች (Ultraviolet Rays) በመጋለጥ የግብርና ምርት መቀነስና የኗሪዎች ጤና መታወክ ሊደርስ ስለሚችል፣

የኦዞን ክምችትን (ozone Layer) ለመንከባከብ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣

ሠ. ሁኔታውን በሚያካክስ ተመጣጣኝ የዕፀዋት ቁስ (Plant Biomass) እስከተተካ ድረስ ለኃይል ፍጆታ የዋለ የዕፀዋት ቁስ ተጨማሪ የአየር ብክላን የማያስከትል መሆኑን መገንዘብ፣ ቋሚ የዕፀዋት ቁስን ለመጨመር የተራቆቱ የደን ቦታዎችን በደን የመሸፈን፣ የእርሻ ደን የማልማት፣ የተሸረሸሩ ቦታዎችን መልሶ እንዲያገግሙ የማድረግ፣ መሬት በዕፀዋት እንዲሸፈን የማድረግ እና በደጋዎቹ አካባቢዎች ልቅ የሆነ ግጦሽን የመቆጣጠር ዕርምጃዎችን መውሰድ፣ ለዚህም የሚያስፈልገውን ገንዘብ የዕፀዋት ቁሱ በቋሚነት በመኖሩ ምክንያት የሚያመነጨት የአየር ብክላ ከሚካካስላቸው በኢንዱስትሪ ከበለፀጉ ሀገሮች መሻት።

## 3.10 ባህላዊና ተፈጥሮአዊ ቅርሶች

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ. የቅርስ እንክብካቤ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አካል ሆኖ እንዲታይና እንዲቀናጅ ማድረግ፣

ለ. የአገሪቷ የቅርስ እንክብካቤ የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ ሆኖ መታየት የሌለበት መሆኑን መገንዘብና የቅርስ ቦታዎችን ወይም አካሎችን በማጥናትና በመሰየም እንዲሁም በመንከባከብ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ቀዳሚ ሚና እንዳለው መገንዘብ፣

ሐ. የቅርስ እንክብካቤ ሥርዓትን ይዘቶችና የርስ በርስ ግንኙነታቸውን እንዲሁም እያንዳንዳቸው ለማኅበራዊና ለኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ሊያገናዘብ የሚችል ዘላቂነት ያለው የቅርስ እንክብካቤና አያያዝ መርሐ ግብር እንዲዘረጋ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

መ. ቅርሶች የሚገኙበት ሥፍራ የተፈጥሮ አካባቢ የቦታውን ውበት፣ ሐውልቶችን፣ ሌሎች ሰው ሰራሽ ቅርሶችን ወይም፣ እንደሁኔታው የፍጡሮች ቅሪቶችን ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ መያዙን ማረጋገጥ።

## 4 የመድበለ ዘርፎች የአካባቢ ፓሊሲዎች

### 4.1 የህዝብ እድገትና አካባቢ

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የእኗኗር ሁኔታ ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ የሥነ ሕዝብ ዕቅድን፣ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝን፣ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ማድረግንና መንከባከብን ማቀናጀት፣

ለ. ሰው ሁሉንም ዕሴቶች ከሞላ ጎደል የሚቀዳጀውና የሥራ ደሲኘሊንንም የሚያዳብረው ገና በልጅነቱ ዘመን ስለሆነ ለልጆች ትምህርትና እንክብካቤ፣ በተለይ ከተፈጥሮ ሀብት ልማትና ዘላቂ አጠቃቀም አኳያ፣ ትኩረት መስጠት፣

ሐ. የድህነት፣ የጤና የትምህርት እና የሕዝብ ሥልጣን (Empowerment) ጉዳዮች ከሕዝብ ዕድገት፣ ሀብትን ከማግኘትና ከማዳረስ እንዲሁም ከአካባቢ ደህንነት ጋር የተሳሰሩ በመሆናቸው፣ በአንድነት መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ማድርግ፣

መ. በፈቃደኝነት ለሚካሄዱ ሠፈራዎች የሚያመቹ ቦታዎችን ለመጠቆም እንዲቻል አጠቃላይና አገር አቀፍ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ የሕዝብ መሸከምን ችሎታ (carrying Capacity) የሚመለከት ጥናት ማካሄድ፣

ሠ. በሕዝብና በአካባቢ ጉዳዮች የውሳኔ አሰጣጥ እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነትና አያያዝ ጉዳዮች ላይ ሴቶች ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችላቸው ሙሉ ሥልጣን መቀዳጀታቸውን ማረጋገጥ፣

ረ. በእርሻ ላይ እንዲሁም ከአርሻ ውጭ የተመሠረቱ ገቢ የሚያስገኙ መርሃ ግብሮችን መዘርጋት፣ እነኝህም መሬት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም በሴቶች ላይና መሬት በሌላቸው ወንዶች ላይ በበለጠ እንዲያተኩሩ ማድረግ፡፡

### 4.2 የማኀበረሰቦች ተሳትፎና አካባቢ

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ከኘሮጀክት ሃሳብ ጀምሮ እስከ ዕቅድ፣ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ድረስ ያሉ የአካባቢና የተፈጠሮ ሀብት ልማት እና አያያዝ ተግባሮች በተፈጥሮ ሀብት ተጠቃሚዎቹና ተንከባካቢዎቹ ውሳኔዎች ላይ ተመሥርተው የሚፈፀሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ለ. በተፈጥሮ ሀብትና በአካባቢ የኤክስቴንሽን መርሐ ግብሮች ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች በህዝብ ተሳትፎ የሚካሄድ ልማትን እንዲያራምዱ የሚያደርግ አዲስ አቅጣጫ እንይይዙ ማድረግና የሣይንሳዊ ምርምርና በየሰፍራው የሚገኙ ገበሬዎች ተመክሮ ውጤቶችን በተሻለና አመርቂ በሆነ መንገድ እንዲያሰራጩ ለማስቻል የሐሳብ ማስተላለፍ /የኮሙንኬዬሽን/ ችሎታቸውን ማጠናከር፣

ሐ. ለአካባቢና ለተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እና አያያዝ ኘሮጀክቶችና መርሐ ግብሮች የዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር የሚመጥኑ አመርቂ የሕዝብ ተሳትፎ ዘዴዎችን መንደፍ፣

መ. በስመ ተሳትፎ የሌሎችን ውሳኔዎች በረቀቀ ዘዴ ማስፈፀምን ለመከላከል እንዲቻል ማኅበረሰቦች ዓቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስፈልገውን የሕግ፣ የሥልጠናና የገንዘብ ድጋፍ መስጠት፣ በተፈጥሮ ሀብትና በአካባቢ አያያዝ ላይ እውነተኛ የማኅበረሰቦቹ አባላት (Grass root) ውሳኔዎች መስጠታቸውን ማረጋገጥ፣

ሠ. ለተፈጥሮ ሀብቶች ልማት፣ አያያዝና ዘላቂ አጠቃቀም ተግባር የሚውል ገንዘብ ለማግኘት እንዲችሉ በየደረጃው ያሉት የተደራጁ አካላት በአካባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚመነጭ ገቢ እንዲያሰባስቡ ሥልጣን መስጠት፣

ረ. በተፈጥሮ ሀብትና በአካባቢ አያያዝ መስክ የተሰማሩ ሴት የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሠራተኞችን ብዛት በከፍተኛ ደረጃ መጨመር፣

ሰ. የመረጃ አሰባሰብና ስርጭት ስርዓትን በመዘርጋት ወደ ላይም ወደ ታችም የሚያመራ የመረጃ ፍሰት በሁሉም ደረጃዎች፣ ማለትም በፌዴራል፣ በየክልሉና በየማህበረሰቡ እንዲዘረጋ ማድረግ፣

## 4.3 የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ይዞታና የተጠቃሚነት መብቶች

ፖሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ማንኛውም ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በአሁኑ ወቅት ሕገ መንግሥቱ የመሬት ተጠቃሚዎች መሬትንና በርሷ የሚገኙ ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶችን (ማለትም ዛፍች፣ ውሃ፣ የዱር እንስሳትና ግጦሽ) በተረጋገጠና በማያቋርጥ ሁኔታ የማግኘት መብት እንዲኖራቸው ያደረገ መሆኑን መገንዘብ፣

ለ. ከሕገ መንግሥቱና ከማኀበራዊ ፍትሐዊነት አንፃር ሲታዩ ተቀባይነት ያላቸው የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት የማግኘትና የመጠቀም ልማዳዊ (Customary) መብቶች በማኀበረሰቦች በኩል ተቀባይነት ያላቸው ከሆኑ በተቻለ መጠን ዕውቅና እንዲያገኙና ጥበቃ እንደደረግላቸው ማድረግ።

## 4.4 የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ

ፓሊሲው የሚከተለው ነው፡-

የፌዴራል፣ የክልልና የማኀበረሰብ ሥልታዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅዶች (Strategic Land use plans) ጠቅለል ያሉ የመሬት አጠቃቀሞችንና የተጠቃሚ ዓይነቶችን ለይተው እንዲያሳዩና አጠቃላይ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ማሻሻያ ሐሳቦችን እንዲዘረዝሩ፣ እነዚሁ ዕቅዶችም የግለሰቦችንና የማህበረሰቦችን ዝርዝር ቀበሌአዊ (Local) የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና አያያዝ ዕቅዶችን ለማዘጋጀት እንደመመሪያ እንዲያገለግሉ ማድረግ።

## 4.5 የማህበራዊና የጾታ ጉዳዮች

ፓሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የአካባቢንና የሀብት አያያዝን አስመልክቶ የሚሰጥ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ሥልጠና፣ ፍትሐዊ ያልሆኑ ሁኔታዎችን ለማወቅና ለማስወገድ የሚያገለግሉ ዘዴዎችን እንዲያካትት ማድረግ፣

ለ. የአካባቢ ግንዛቤና የሕዝብ የትምህርት መርሐ ግብሮች በሁሉም ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ የኀብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ያሉትን ወንዶችንም ሴቶችንም እንዲያሳትፉ ማድረግ፣

ሐ. በተወሰኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ብሔረሰባዊ፣ ማኀበራዊ፣ ባህላዊ፣ ጾታዊና የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ የኀብረተሰብ ክፍሎች፣ በተለይም ለተጐዱት፣ እኩልነትን ለማስፈን እንዲቻል ፓሊሲዎች፣ መርሐ ግብሮችና ኘሮጀክቶች ሁሉ የተፅዕኖ ግምገማ ጥናት (Impact Assessment) እንዲካሄድባቸው ማድረግ፣

መ. በሥልጠና፣ በንቃት መርሐ ግብሮች፣ መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ትምህርት እና በአካባቢና በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ውሳኔ አሰጣጥ በሁሉም የኅብረተሰቡ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ሴቶች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

## 4.6 የአካባቢ ምጣኔ ሀብት

ፖሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የአካባቢ ወጪዎችና ጥቅሞች፣ የአካባቢ መሻሻልንና መጐሳቆልን እንዲያካትቱ አድርጎና ሳይገኙ የሚታለፉ ጥቅሞችን ከወጪ ጋር ጨምሮ፣ በመርሐ ግብርና በፕሮጀክት ዝግጅት እንዲሁም ልማትን በማቀድ ሂደት ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ፣

ለ. በትክክለኛ መረጃ ዕጦትና ተቀባይነታቸው የተረጋገጠላቸው የአቀማመር ስልቶች (Standardized methodologies) ባለመኖራቸው የተነሳ የአካባቢ ወጪዎችና ጥቅምች ግምት ብዙውን ጊዜ ትክክለኛ ሊሆን አለመቻሉን በመገንዘብ በወቅቱ ሻል ብለው በተገኙ መረጃዎችና የአቀማመር ስልቶች በመጠቀም የእነዚህ ወጪዎች ስሌት በሂሳብ አያያዝ ውስጥ እንዲካተት ማድረግ፣

ሐ. የአካባቢ ተፅዕኖ ውጤቶች ረዥም ጊዜ (በአብዛኛው በዓስርት ዓመታት የሚቆጠር) የሚወሰዱ መሆናቸውን በመገንዘብ በኢኮኖሚ ትንተና ውስጥ ታሳቢ የሚሆኑ የጊዜ ወሰኖችን (Time Frame) በዚያው መጠን ማራዘም፣

መ. የአካባቢ ሂሳብ አያያዝን በኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግን ለመጀመር የሙከራ ፕሮጀክት ማካሄድ፣

ሠ. ዋና ዋና የልማት መርሐ ግብሮች፣ ፕሮጀክቶችና የሥራ እንቅስቃሴዎች ሲታቀዱ የአካባቢ የኢኮኖሚ ወጪዎችና ጥቅሞች ስሌትን በ5፣ 10፣ 50፣ እና በ100 ዓመታት የጊዜ አድማሶች ውስጥ ማካሄድ፣

ረ. የተፈጥሮ ሀብትን ወይም አካባቢን ለዘለቄታው ጠብቆ ለማቆየት እንዲቻል አግባብ ያላቸው የተጠቃሚዎች ክፍያዎችንና (Appropriate Level of User and Access Fees) የአፈፃፀም ዋስትና ክፍያዎችን (Performance bonds) ወደ ፓርኮች ለመግባት፣ በተከለሉ የግጦሽ ቦታዎች ለመጠቀም፣ በውሃ ለመጠቀም፣ ከደን ዛፍ ለመቁረጥ፣ ወዘተ መጠየቅና የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ አጠቃቀም

ዘላቂነት እንዲኖረው ትክክለኛ ተጠቃሚዎችን ለይቶ ታክስ እንዲከፍሉ፣ ከታክስ ለተወሰነ ጊዜ ነፃ እንዲሆኑ ወይም ድጎማ እንዲያገኙ ማድረግ፣

ሰ. የተጠቃሚዎችን ክፍያዎችና የማትጊያ ጥቅሞችን ፋይዳ ለመተንተን እና ውሎችን፣ ኪራዮችን፣ የማልማት መብቶች (Concessions) እና የአፈፃፀም ዋስትና ክፍያዎችን ለመከታተልና ዘላቂነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና የአካባቢ ጥበቃ እንዲኖር ለማድረግ እንዲችሉ የመንግሥት ድርጅቶችን አቅም መገንባት፡፡

## 4.7 የአካባቢ መረጃ ስርዓቶች

ፖሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. በንፁህና በጤናማ አካባቢ የመኖር መብት ስለ አካባቢ ጉዳዮች መረጃ የማግኘት መብትን ማካተት እንዳለበት የሚገልፀውን መርህ መከተል እንደሚያስፈልግ ማወቅና ተገቢ የመረጃ ሥርዓትን መዘርጋት፣

ለ. የማህበረሰብ የአእምሮ ውጤት ባለቤትነትን የሚጠብቅ ሥርዓት በሕግ እንዲወጣ ማድረግ፣

ሐ. ሥርጭቱ ብሔራዊ ደህንነትን፣ የማኅበረሰብ የአእምሮ ውጤት ባለቤትነት መብቶችን (Community Intellectual Property Rights) ወይም የግል የአእምሮ ውጤት ባለቤትነትን (Intellectual Property Rights) የሚነካ ካልሆነ በስተቀር የአካባቢ መረጃ ለሚፈልጉት ሁሉ እንደ ሕጋዊ መብት ሆኖ እንዲዳረስ ማድረግ፣

መ. መረጃ የማመንጨት ተግባር የተጠቃሚዎችን ፍላጎቶች ለይቶ በማወቅ ላይ ተመሠረተ ማለትም የተጠቃውን ጥያቄ የሚያሟላ (Demand- driven) እንዲሆን ማድረግ፣

ሠ. የአካባቢ መረጃ አሰባሰብና ትንተና እንዲሁም የመረጃ ሥርጭት ያልተማከለ ነገር ግን የተቀናጀ እና በተቻለ መጠን ደረጃው አንድ ወጥ የሆነ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ. በስፋት በጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎች ሊገኙ የሚችሉበትና ለልዩ ተጠቃሚዎች የተዘጋጁ (Specialized) መረጃዎች የሚገኙባቸው ቦታዎች የሚረጋገጡበት ማዕከላዊ ቦታ ወይም ድርጅት እንዲኖር ማድረግ፣

ሰ. የአካባቢ መረጃ ማመንጨት፣ መሰብሰብንና ማሠራጨትን የሚመለከቱ ሕጎችና መመሪያዎች እንዲኖሩና አስፈላጊ የሚሆኑ እገዳዎች እንዲገለፁ ማድረግ፡፡

### 4.8 የአካባቢ ምርምር

ፖሊሲዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ላይ ተጽዕኖ የሚኖራቸውን ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቴክኒካዊ ሁኔታዎችን በመጠቆም ላይ መርጦ የሚያተኩር ሥልታዊ ምርምር መቅረፅ፣

ለ. ተማራማሪዎች በቴክኒክ ሙያቸው እንዲልቁና በምርምር ውጤቶቻቸው ከተጠቀሙበት የግብርና ሥርዓተ መሕድራዊ፣ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር እንዲተዋወቁ ለማስቻል ስልጠና መስጠትና የስራ ሁኔታዎችን ማሻሻል፣

ሐ. በገበሬዎች፣ በእንስሳት አርቢዎች፣ በመንግሥት ባለሙያዎች፣ በልማት ሥራ በተሠማሩ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በተመራማሪዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅርብ ግንኙነት የሚያመቻች፣ ተገቢ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትና መዋቅር እንዲኖር ማድረግ፣

መ. ሣይንቲስቶች ባላቸው ጠቅላላ (Universal) የሣይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት እንዲሁም ተጠቃሚዎች ስለአካባቢያቸው ባላቸው ብቸኛና የተለየ (Unique) ዕውቀት ቅንጅት ለመጠቀም እንዲቻል ለአካባቢ አያያዝና ለዘላቂ ልማት ተገቢ እንዲሆኑ በታለሙ ቴክኖሎጂዎች ላይ የሚደረግ ምርምር በሣይንቲስቶችና በምርምር ተጠቃሚዎች መካከል በጋራ እንዲካሄድ የሚያደርግ ሁኔታ ማመቻቸት፣

ሠ. አሁን ያሉት ባህላዊ የምርምርና የትምህርት ሥርዓቶች ዘመናዊውንና ባህላዊውን ወደሚያካትት አዲስ ሥርዓት ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ፣

ረ. ለሥልታዊ፣ ለተግባራዊና (applied) ለማስማሚያ (adaptive) የምርምር መርሐ ግብሮችና ኘሮጀክቶች ድጋፍ ለመስጠት የምርምር ገንዘብ እንዲመደብ ማድረግ፣

ሰ. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማህበራትን በየማህበረሰቡ ማቋቋም፣ የየማህበረሰቡን ባህላዊ (Traditional) የምርምርና የልማት ሥርዓቶች ለይቶ በማወቅ መደገፍ፣ እንዲሁም የምርምር ግኝቶች ተስማሚ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን በሚመለከት መረጃ ሊተላለፍ የሚችልበትን መስመር መፍጠር፣

### 4.9 የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ

ፖሊሲዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በግዑዛዊና በሥነ ሕይወታዊ ሁኔታዎች ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎችን ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎችንም የሚያካትት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ. የመንግሥትና የግል ዘርፍ የልማት መርሐ ግብሮችና ፕሮጀክቶች ማንኛውንም የአካባቢ ተፅዕኖዎች ቀደም ብለው በመገንዘብ፣ የመከላከያ እርምጃዎችን በልማቱ አነዳደፍ ሂደት ውስጥ ማካተታቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ. ከሕዝብ ጋር የሚደረግ ምክክር ከአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ተግባር ተነጥሎ ሊታይ የማይችል መሆኑን መገንዘብና የአካባቢ ተፅዕኖ ሂደትም አንድ ጉዳይ ለውሳኔ ሰጪዎች ከመቅረቡ በፊት በገለልተኛ አካል መመርመሩንና የሕዝብ ትችት ማካተቱን ማረጋገጥ፣

መ. በማንኛውም ጊዜ የአካባቢ ተፅዕኖ መግለጫ (EIS) የአካባቢ አያያዝ ችግሮች የሚቃለሉበት እንዲሁም ድንገተኛ ሁኔታ ወይም አደጋ ሲፈጠር የሚያገለግሉ የመከላከያ ዕቅዶችን ማካተቱን ማረጋገጥ፣

ሠ. በአካባቢ ተፅዕኖ መግለጫው ተፈላጊነታቸው ለታመነባቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች በፕሮጀክት አፈጻጸም ወቅት በተወሰኑ ጊዜያት ክትትልን፣ ቁጥጥርንና የዘገባ አያያዝን የሚመለከት የአካባቢ ኦዲት መካሄድን ማረጋገጥ፣

ረ. የቅኝትም ሆነ ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎች፣ የመንግስት ከሆኑ በሚመለከታቸው መንግስት መ/ቤቶች፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ከሆኑ ደግሞ በአልሚው ባለሀብት መከናወናቸውን ማረጋገጥ፣

ሰ. ለግልና ለመንግሥት ፕሮጀክቶች ተገቢ የሆኑ የአካባቢ ተፅዕኖ መግለጫዎችና የአካባባቢ ኦዲቶች መካሄድ እንዳለባቸው የሚያረጋግጥ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሥርዓትን በሕግ ማውጣት፣

ሸ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለማካሄድ፣ ለማቀናጀት፣ ለማጽደቅና ከዚያ በኋላም የአፈፃፀም ገደቦች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ኦዲት ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ተቋማዊ ማዕቀፍ መዘርጋትና የማዕቀፉ የተለያዩ ክፍሎች ሊኖራቸው የሚገባውን ትስስር መወሰን፣

ቀ. ለአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና ኦዲት የሚያገለግሉ ዝርዝር ዘርፋዊ መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣

በ. ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ሁኔታዎች በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የአሠራር ሥርዓት ውስጥ መካተታቸውን እና በዘርፍ መመሪያዎች ውስጥ መግባታቸውን ማረጋገጥ፣

ተ. በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ በአስፈጻሚ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች፣ እንዲሁም በክልሎች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እና የአካባቢ ኦዲት ተግባራትን የማከናወን አቅምንና ችሎታን ማጐልበት።

## 4.10 የአካባቢ ትምህርትና ግንዛቤ

ፖሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. በሦስተኛው የትምህርት ደረጃ (Tertiary Level) ላይ ለብቻው መስጠት ቢኖርበትም በሌሎች ደረጃዎች ግን የአካባቢ ትምህርትን ለብቻው ወይም እንደተጨማሪ ትምህርት ሳይሆን፣ በመድብለ ዘርፍነት (Multidisciplinary) መስጠትና በትምህርት ቤቶችና በኮሌጆች ሥርዓተ ትምህርቶች ውስጥ ተቀናብሮ እንዲካሄድ ማደረግ፣

ለ. የአካባቢ ትምህርትና የግንዛቤ መርሐ ግብሮች ትኩረት በህዝቡ፣ በተለይም በአካባቢ ላይ የጐላ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ በሚችሉ የመንግሥትና የግል ዘርፍ የሥራ እንቅስቃሴዎች፣ ላይ እንዲሆን ማድረግ፣

ሐ. በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የአካባቢ ሁኔታዎችና ችግሮች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን፣ የአካባቢ ግንዛቤ መርሐ ግብሮች ሲቀረፁ በየስፍራው በሚገኙ ዓይነተኛ የአካባቢ ችግሮች ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፣

መ. በኢትዮጵያ ካለው የመገናኛ ችግር አንፃር የመገናኛ ብዙሃን መጫወት የሚችሉትን ከፍተኛ ሚና በመገንዘብ የአካባቢ ግንዛቤ መርሐ ግብሮችን በማዘጋጀትና በማስፋፋት ረገድ በአግባቡ እንዲሰማሩ ማድረግ፣

ሠ. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ አያያዝን የሚመለከቱ መርሐ ግብሮችንና ስልጠናዎችን ለኢኮኖሚስቶች፣ ለዕቅድ አውጪዎች፣ ለሕግ ባለሙያዎች፣ ለመሐንዲሶች፣ ለሶሲዮሎጅስቶች፣ ለሕክምና ባለሙያዎችና እንዲሁም ለተፈጥሮ

ሀብትና አካባቢ ሣይንቲስቶች ለመስጠት እንዲቻል አሁን ያሉትን ከፍተኛ የሥልጠናና የትምህርት ተቋማትን ማጠናከር፣

ረ. በአካባቢ ኢኮኖሚክስ፣ በአካባቢ ሕግ፣ በአካባቢ ክትትል፣ በመልክዐ ምድር የመረጃ ሥርዓት (GIS) በብክለት ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም በአደገኛ ንጥረ ነገሮች አያያዝ (Hazardous waste Management)፣ የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፣

ሰ. የቀበሌ የአካባቢ ግንዛቤ ማህበራት ዕድገትንና ለተለያዩ የግብርና ቀጠናዎች (የግብርና ሥርዓተ መሕድሮች) አግባብነት ያላቸው መርሐ ግብሮች መዘርጋትን ማበረታታት እንዲሁም በሳይንሳዊ ግብአቶች መደገፍ፣

ሸ. በመገናኛ ብዙኃን የሚሰራጨው በከተሞች ሁኔታ ላይ የሚያተኩሩ የግንዛቤ መርሐ ግብሮችን ማዘጋጀትና የከተሞች የአካባቢ ግንዛቤ ማህበራት እንዲቋቋሙ የሚያግዝ ሁኔታ መፍጠር፣

ቀ. የማኅበረሰቦችና የሃይማኖት መሪዎች የአካባቢ ግንዛቤን እንዲያራምዱ በሚዘረጉ መርሐ ግብሮች እንዲሳተፉ ማነሳሳት፣ ማበረታታትና ማገዝ።

# 5 የፖሊሲ አተገባበር

## 5.4 መዋቅር፣ ኃላፊነትና የሥራ ድርሻ

ፖሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. በፌዴራል፣ በክልል በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ማኅበረሰብ ደረጃዎች ውጤታማነትን ለማስመዝገብ፣ የተፈጥሮአዊ፣ የሰው ሠራሽ እና የባህላዊ ሀብቶች ዘላቂ አጠቃቀም ፖለቲካዊና ሕዝባዊ ድጋፍ እንዲያገኝ ማድረግ፣

ለ. ከፌዴራል እስከ ማኅበረሰብ ደረጃ ባሉት እርከኖች የሚገኙ በህግ የተቋቋሙ አስተባባሪና አስተዳዳሪ አካላት፣ እንደ መዋቅር እርከናቸው አግባብነት፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ የኮሚሽኖች፣ የባለሥልጣኖች የቢሮዎችና በተጨማሪም የክልልና የከተማ መስተዳድሮች፣ ተመራጭ የምክር ቤቶች አባላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣የማኅበረሰብ ተወካዮች፣ የባለሙያዎች ወይም ሌሎች አካባቢን የሚመለከቱ ማኅበራት እና የግሉ ዘርፍ ኃላፊነቶች በመሆን ተለይተው የታወቁ የዘርፍና የመድብለ ዘርፍ የዕቅድና የአፈፃፀም ጉዳዮችን ማስተናገዳቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ. በተቻለ መጠን አሁን ባሉ የተቋም መዋቅሮች መገልገል፣

መ. ለእንክብካቤና ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና አያያዝ ሥልቶች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ ክትትልና አፈፃፀም የሚያስፈልገው ተቋማዊ አደረጃጀት ከዚህ በታች በሰፈሩት የመመዘኛ ነጥቦች የሚወሰን እንዲሆን ማድረግ፣

i. ከሕገ መንግሥቱ ጋር መጣጣም፣ በተለይም የሥልጣን አለመማከልን (Decentralization) በሚመለከት፣

ii. የዘርፎችን ፍላጐቶች ማጣጣም፣

iii. የአካባቢ ዘርፍ ዕቅድን ከልማት ዕቅድ ጋር ማዋሀድ፣

iv. የተጨማሪ ፋይናንስ ፍላጎትን በተቻለ መጠን ማሳነስ፣

ሠ. በአንድ በኩል የአካባቢና የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አያያዝ የሥራ እንቅስቃሴዎች፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥርና ክትትል ተግባራት እንዳይጋጩ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ኃላፊነትን ለተለያዩ ድርጅቶች በመስጠት የአሠራር ግጭቶችን ማስወገድ፣

ረ. የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የመንግሥት ሕጎችንና ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶችና መስተዳድሮች መሆኑን ማረጋገጥ፣ ሆኖም የመንግሥት የልማት እንቅስቃሴዎች በሕጎችና በደንቦች መሠረት ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሲሆን፣ የሚኒስቴር መ/ቤቶችና ሌሎች በመንግሥት ሥር የተዋቀሩ አካላት መመሪያዎችን ተከትለው መሥራታቸውን ለማረጋገጥ የሚካሄደው ክትትል የአካባቢ ጥበቃና የቁጥጥር ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት ድርጅት መካሄዱን ማረጋገጥ፡፡

### 5.5የህግ ማዕቀፍ

ፖሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ለተፈጥሮአዊ፣ ለሰው ሠራሽና ለባህላዊ ሀብቶችና ለአካባቢ ዘላቂ አጠቃቀምና አያያዝ የሚያገለግሉ የፌዴራልና የክልል ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችንና ዕቅዶችን በመቅረጽ ሂደት የኢትዮጵያ ሕዝብን ተሳትፎ የሚያበረታታ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፣

ለ. የአገራቷን ተፈጥሮአዊ፣ ሰው ሠራሽ፣ ባህላዊ ሀብቶችንና አካባቢን እንዲያንሰራሩ ለማድረግ፣ ለመጠበቅ፣ ለማስተዳደር እና ዘላቂ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል የኢትዮጵያን ሕዝቦች የሚያነሳሱ መርሐ ግብሮች እንዲዘረጉ ማድረግ፣

ሐ. ከሕገ መንግሥቱና ከወቅታዊ የፖለቲካ፣ የማኀበራዊ፣ የባህልና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ህጐችና አሰራሮች ጋር ስምምነት መኖሩን ማረጋገጥና ከዘላቂ ልማት መርህ ጋር ማጣጣም፣

መ. የህገ መንግስቱን አንቀጽ 44 በመከተል፣ በአገሪቷ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ለጤናቸውና ለደህንነታቸው ብቁ የሆነ አካባቢ የማግኘት መሠረታዊ መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ፣

ሠ. የተፈጥሮአዊ፣ የሰው ሠራሽና የባህላዊ ሀብቶች እንዲሁም የአካባቢ ማንሰራራትን፣ መጠበቅን፣ማስተዳደርንና በዘላቂ መንገድ መጠቀምን የሚመለከቱ ዘርፋዊ ደንቦችንና የአሠራር መመሪያዎችን ለማዘጋጀት፣ ለመመርመርና ለመከለስ የሚያስችሉ አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

ረ. የቅጣትና የማበረታቻ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያገለግል አጠቃላይ ማዕቀፍ ማውጣት፡፡

## 5.6 ክትትል፣ ግምገማና የፖሊሲ ክለሳ

ፖሊሲዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. እያንዳንዱ መርሐ ግብርና የኘሮጀክት ክትትል ተግባር ተገቢ የሆኑት የፌዴራል ወይም የክልል አስፈጻሚ አካላት ወይም ሥልጣን የተሰጣቸው ድርጅቶች ኃላፊነት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ. የአካባቢ ፖሊሲው አፈፃፀም በአገሪቱ ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች (Renewable Natural Resources) እና አካባቢን በሚደግፉ ሥርዓቶች ላይ የሚኖረው አጠቃላይ ውጤት ክትትል የሚደረግበት መሆኑንና ከክትትሉ የሚመነጩ የማሻሻያ የውሳኔ ሀሳቦች (Recommendation) የማጠናቀር ሂደትም ከህዝብ ለተሰጡ አስተያየቶች ምላሽ የሚሰጥና በኢትዮጵያ የእንክብካቤ ስልት ሰነዶች ውስጥ ከተቀመጠው ተቋማዊ መዋቅር ጋር የሚስማማ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ. የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የዚህን ፖሊሲ አጠቃላይ አፈፃፀም የሚከታተል መሆኑንና እንዲሁም ሥልጣን ከተሰጣቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር እና/ ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ማህበረሰቦችና ቡድኖች አስተያየት ከግምት ውስጥ በማስገባት የማሻሻያ ሀሳቦችን የማፍለቅና እነዚህም ሀሳቦች በበይነ ሚኒስቴራዊው የአካባቢ ጥበቃ ጉባኤ እንዲፀድቁ የማድረግ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ. አስፈፃሚ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና እንዲሁም የክልል እና ከዚያ በታች ያሉ ቢሮዎችና ቅርንጫፎቻቸው እንዲከታተሏቸው ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጣቸው የሥራ ዘርፎችና ክፍሎች ላይ የዚህ የአካባቢ ፖሊሲ አፈጻጸም የሚኖረውን አጠቃላይ ውጤት መከታተላቸውን ማረጋገጥ፣

ሠ. የተፈጥሮ ሀብቶችና የአካባቢ ሁኔታ ግምገማዎች፣ የዚህን ፓሊሲ አፈፃፀም ጨምሮ፣ ከማህበረሰብ የአካባቢ አስተባባሪ ኮሚቴ በመነሳትና በየደረጃው አግባብ ባላቸው የውሃ ሀብት፣ የማዕድንና የኢነርጂ፣ የግብርና እና የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ቢሮዎች አማካኝነት ወደ ላይ እየተጠቃለሉ በየዓመቱ መከናወናቸውን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የዘገባዎቹን መጠናቀር ሂደት ለመገፋፋትና በሂደቱም ላይ ዘገባ ለማቅረብ የሚያስችለው ኃላፊነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ. ቢያንስ በየዓመቱ በመንደር ደረጃ ማኀብረሰቡ ከአካባቢ አስተባባሪ ኮሚቴዎቹ ጋር በመሆን ከዚያም በተከታታይ ከወረዳና ከክልል የአካባቢ አስተባባሪ ኮሚቴዎች እስከ አካባቢ ጥበቃ ጉባኤ ደረጃ ድረስ ስብሰባዎች መካሄዳቸውንና እነዚህም ስብሰባዎች በግምገማ ውጤቶች ላይ ውይይት ማካሄዳቸውን ማረጋገጥ፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ውይይቶቹ መካሄዳቸውን የማረጋገጥና ስለ ውይይቶቹም ሂደት ዘገባ የማቅረብ ኃላፊነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ።